# እስልምና ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ራእይ ጋር አይስማማም፤ አይቀበለውምም

ቀደም ብለን በገጽ 25 እንዳነበብነው የእስልምና ተስፋ

> «ስለ ክርስቲያናዊ ንድፈ አሳብ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መባሉ፥ ስለ መሢሑ የመስቀል ዝክረ- ሐተታ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰው ልጅ ደኅንነት ስለ ማግኘቱ... ድጋፍና ነቀፋ ለመስጠት የሚረዱ እስላማዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ለይቼ ለማሰባሰብ» ነው።

ቢያንስ በሙስሊሞች መካከል፥ እስልምና ይህን በማድረግ ስኬታማ ሆኖ መስንበቱን ስንገልጥ ኃዘን እየተሰማን ነው። የምናዝነውም ይህ በመለኮታዊ መረጃ በልጽጎ የተገለጠውን እውነት የማጥፋት ጥረት በመሆኑ ነው።

ከእስልምና ክሶች በተቃራኒ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ጊዜ ጣልቃ-ገብ ነገሮች እንዳልነበሩበትና የአዲስ ኪዳንም መጻሕፍት በአንድ ላይ ከተጠረዙበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ለውጥ እንዳልተደረገበት የታወቀ ነው። ይህ ሺህ ጊዜ ሊረጋገጥ የሚችል እውነት ነው። ደግሞም ቀደም ብሎ (ገጽ 54-55) ተመልክቷል። እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ውስጥ ያለችውን ቅዱስ እጅ ለማረጋገጥ ትንቢታዊ ገጽታዎችን ተመልክተናል (ከገጽ 59 ጀምሮ)። ምንም እንኳ ቃል በቃል እየተናገረ በማጻፍ ፈንታ፥ እግዚአብሔር በመልእክቱ አሳቦች ሰዎችን ለመሙላት ቢመርጥም፥ መልእክቱ አለ ጥርጥር ማጠናከሪያ እንዳገኘ አስቀምጠናል። አሁንም ወደ በኋላ ሌላ መረጃ ይቀርባል። በእስልምና የተተወውንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ዕቅድ በማጥናት፥ ምንም እንኳ ሁለት ኪዳኖችን ቢይዝ (ብሉይና አዲስ ኪዳኖች ሲሆኑ፥ አንዱ ከአይሁዶች ጋር የተደረገ ብሔራዊ ውል፥ ሌላው ለእግዚአብሔር የይቅርታ ስጦታ ራሳቸውን ለመስጠት ከሚፈቅዱ ሁሉ ጋር)፥ በ66 «መጻሕፍት» ቢጻፍና፥ በ1600 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ 40 በሚሆኑ ሰዎች ቢዘጋጅም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ፍጹም የሆነ የአሳብ መያያዝና ዕድገት እናገኛለን። ይህ መያያዝ አከራካሪነት ላይ በሚገኙት በእነዚህ ትምህርቶች አንፃር ሊብራራ ይችላል፡-



1. ስርየት
2. ኢየሱስና የ«ሥላሴ» አንዱ አካል በመሆን መለኮታዊነቱ፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅነቱ
3. ስቅለት

አሁንም የመከራከሪያ ጥቅሶች የተወሰዱት በሚስተር ጁማል ከተዘጋጀው መጽሐፍ ነው።

## በስርየት ትምህርት ላይ የእስልምና ተቃውሞ

ስርየት ምንድነው? ቃል ኪዳኑን ወይም ከሰው ጋር የገባውን ውል በማፍረስ በእርሱ ላይ ካመፁ በኋላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ማለት ነው። ዓመፁንም ኃጢአት ብለን እንጠራዋለን። ለነገሩ ማንኛውም በአሳብ፥ በቃል፥ ወይም በተግባር ከቃሉ፥ ለሰው ካለው ሕጉና ዓላማው በተጻራሪ የተደረገ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው። ሁሉም ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ዓመፅን በማድረጉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አጥቷል። ይህም የሚያስከትለው ሞትን ለዚያውም መንፈሳዊን ሞት ነው። የዚህም ውጤት ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለዓለም መለያየት ነው፡-

> «ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፡- በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ» (2ኛ ቆሮንቶስ 6፡ 14-16)።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኃጢአት ከተሠራ በኋላ (በፍላጎት አይደለም ዘሌዋውያን 4፡2) ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ኃጢአተኛው ለኃጢአቶቹ ማስተሰርያ ማቅረብ እንዳለበት አዝዟል። የአቀራረቡ ሥርዓትም በብዙ ዝርዝር ተነግሯል (ዘሌዋውያን ምዕራፍ 1-7፥ 16፥ ወዘተ...)። ይህም መሥዋዕትን ማቅረብ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ

የእንስሳ መሥዋዕትነት ለኃጢአተኛው ሲል በተሠቃየው በኢየሱስ ተተክቷል።

አንድ ሙስሊም የሚመለከተው መሠረታዊ ችግር በእግዚአብሔር የስርየት ሥራ ውስጥ ንስሐ ለሚገባው ኃጢአተኛ በእርሱ ምትክ ሌላ የመሠዋቱ ጉዳይ ነው። በኃጢአተኛው ምትክ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል፤ በምትኩም ላይ ትክክለኛ የሆነ ቅጣት ይፈጸምበታል። ሙስሊሞች በጥፋተኛው ምትክ ንጽሑን ሰው መቅጣት የእግዚአብሔርን የፍርድ ሚዛን ያዛባዋል ብለው ይከራከራሉ። ጥፋተኛው የመከራ ምላሽ ሊቀበል እንደሚገባው ሁሉ፥ ትክክለኛውም ሰው የመልካም ነገር ሽልማት ሊሰጠው ይገባል። ስለዚህ ትክክለኛውና ጻድቁ ኢየሱስ በእርግጥ መከራ ሊቀበል አይችልም፤ ይልቁንም እርሱን ለኃጢአተኞች እንዲሠቃይ ማድረግ ለእግዚአብሔር የማይቻል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ይህ ለእግዚአብሔር የጽድቅና ፍትሕ ጽንሰ-አሳብ ዕንቅፋት ይሆናል። ዳሩ ግን ይህ ክርክር ከቁርዓንም ጋር የሚቃረን ነው። በዚያ ውስጥ የጥንት ነቢያት መከራ እንደ ተቀበሉና እንደ ተገደሉ ይናገራል (ሱረቱ 3፡ 183)።

መሐመድ ራሱ በአንድ አጋጣሚ ለሞት እስኪያጣጥር ድረስ (ከዚህ የተነሣ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደ ተሠቃየ ሃዲስ ይናገራል) ከተደረገበት መርዝ የተነሣ ስለ ተሠቃየና በኡሑድ ጦርነትም የሸንፈትን ጽዋ በመጎንጨት መከራ ስለ ተቀበለ (እርሱ ራሱ ከፊቱ ላይ ቆሳስሏል፤ ሁለት የፊት ጥርሶቹም ረግፈዋል)፥ እዚህ ላይ ከሙስሊም የሃይማኖት መሪዎች ያጋጠመን ክርክር እንዲሁ ለመናገር ያህል የቀረበ ነው ብንል ከእውነት አንርቅም።

በተጨማሪም አላህ አል-ራህማን እና አል-ራህም (ጸጋን የተሞላና መሐሪ) ተብሎ የሚጠራበትን «ብስሚላሂ»ን መጥቀስ አለብን። ጸጋ የማይገባ ስጦታ ነው። በሕጋዊ አነጋገርም ይቅርታ ማለት ነው። ምሕረት ሰውየው መረዳት ይገባው ወይም አይገባው እንደ ሆነ የማይመለከት የርኅራኄ ተግባር ነው። ይህ በእርግጥ ግብታዊ የሆነ እርዳታ ነው።

ይቅርታ ወይም የስርየት ተግባር የቃሉን ትርጉም በትክክል ከተጠቀሙበት ፍትሕ-አልባ ነው። ለተላላፊው አይገባውም። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር (ጽድቁን ለማርካት) የኃጢአት ተግባር የሚቀጣበትንና



ኃጢአተኛው የሚመለስበትን መንገድ አሰናድቷል። ስርየት ማለት እንግዲህ ይኸው ነው። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የሚከተለውን ቃል መቀበል መቻል አለብን፡-

> «አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና፥ ይላል እግዚአብሔር። ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው» (ኢሳይያስ 55፡8-9)።

እግዚአብሔር የሚወዳቸውንና የሚወዱትን ለማዳን ዕቅድ በሚወጥንበት ጊዜ አንድም መቀበል፥ አሊያም መተው አለብን። እግዚአብሔርንና የተገለጸውን መንገዱን፡-

> «እግዚአብሔር እንዴት እንደዚያ ሳይሆን እንደዚህ አደረገ?»

ብለን በመከራከር ልንጠይቀው አንችልም። ለመሆኑ ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወይም ለመምከር እኛ ማን ነን? ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር ከእግዚአብሔር የተገለጹ እንደ ሆኑ እየተናገሩ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ያላቸውን በመመርመር እውነት በሆነው ነገር መኖር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ጻድቁን ለመከራ አሳልፎ እንደማይሰጥ የሚናገረው የእስልምና ጽንሰ-አሳብ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን የስርየት ሥራ ዋጋ በማሳጣት የገዛ ጥቅማቸውን ለመጠበቅ የሚደረግ ክርክር እንደ ሆነ ለመገመት እንገደዳለን።

ሁል ጊዜም ሙስሊሞች በተሳሳተ መንገድ እንደሚከተለው ያስባሉ፡-

> «ይህ ትምህርት ለሰው ልጅ ላይገታ እንደ ልብ ኃጢአት ለመፈጸም ፈቃድ ይሰጣል። አንድ ሰው ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር ያለፈውና የወደፊቱ የሰው ልጆች ኃጢአቶች ታጥበው እንዲነጹ ባደረገው በኢየሱስ ደም ላይ ጭፍን እምነት መጣል ነው። ይህ ለመከተል እጅግ ምቹ፥ ተስማሚና ቀላል ትምህርት ነው። ከአማኙ የሚጠይቀው ምንም ጥብቅ ወይም ተግባራዊ የአምልኮ ዓይነት

የለም። ዝም ብሎ ማመን ብቻ ሲያስፈልገው፥ ደኅንነቱም በዚያው ይረጋገጥለታል» (ኤ.ኤስ.ኬ. ጁማል)።

በእነዚህ ቃላት ውስጥ የራስን ደኅንነት ለማስተዋወቅ የሚደረግ ጥረት እንመለከታለን። ይህ ይቅርታ የሌለው ኃጢአት ነው። ምክንያቱም ይህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተፈጸመ ኃጢአት ነው። ሰው በራሱ ኃጢአቱን ለማስወገድ ብቁ የሆነ ይመስለዋል። ይህን ጭብጥ ወደ ትክክለኛ መደምደሚያው ስንወስደው፥ ሰው በራሱ «ደጋግ ሥራዎች» በማካካስ ወይም «ጥብቅ የአምልኮ ዓይነት» በማድረግ ለሠራቸው ኃጢአቶች መፍትሔ ለማግኘት ስለሚችል፥ ሰው እግዚአብሔርን አይፈልገውም ማለት ይሆናል። «የአምስቱ የእስልምና አእማድ» ዓላማ ይኸው እንደ ሆነ እናስባለን። ይሁንና ደግ ሥራ መሥራት ኃላፊነታችን ነው። ይህን በማድረግ ግን የሚመጣ ትርፍ የለም። ለኃጢአታችን ደግ ሥራ በመሥራት ለማካካስ የምንፈልግ ከሆነ፥ ጽድቅን ለራሳችን ያዘጋጀነው እኛው ነን ማለት ነው። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ «ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው» (ኢሳይያስ 64፡6) ይላል።

ችሎት የቀረበ ወንጀለኛ ደግሞ ያንን ጥፋት እንደገና እንደማይፈጽም ወይም ለወደፊት «ደግ ሰው» ለመሆን ቃል በመግባቱ በነጻ ስለ መለቀቁ ሰምተህ ታውቃለህ?

ሰውሩ ችግር ያለው ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ «ኃጢአት» ለሚለው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጽንሰ-አሳብ እጅግ የተለየ አመለካከት ከመያዛቸው ላይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአት የተመለከተው የሰውን ልጅ ሁሉ ባሪያ የሚያደርግ እና ሁሉንም ሰው ኃጢአትን ወደ መሥራት የሚገፋፋ መምሪያ ሆኖ ነው። እንደ መግደል ያለ «ትልቅ ኃጢአት» ወይም በንግድ ላይ ውሸትን እንደ መናገርና ከሱባንያ ውስጥ አንድን ነገር እንደ መስረቅ ያለ «ትንሽ ኃጢአት» ቢሆን፥ ኃጢአት የሰው ከጥገኝነት ነጻ የመሆን ዝንባሌ፥ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ግልጽ ዓመፅ ነው። ሁለቱም በሰው ፈቃድ እና ሕሊና ውስጥ ማዕከላዊው ስፍራ ለእግዚአብሔር አለመሆኑን ያስቀድማሉ። ምናልባት በርካታ ሃይማኖታዊ ግብሮችና መስጠት ቢኖረውም የአምላኪው ታማኝነት ባመዛኙ በሥራው ፍሬ-ከርስኪ ይሆናል። እነዚህን ኃጢአቶች ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ



በማሽከርከራችን እንደሚሰጠን የቅጣት ትኬት አድርገን ልንወስዳቸው አንችልም፤ ኃጢአት እኛን ከእግዚአብሔር ይለየናል!

«በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቍጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን . . . ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌሶን 2፡1-5፥ 8-10)።

ሃያሲያን እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ክርስቲያን እንደ ሆነና ንስሐ (ከኃጢአት መመለስ) አንድም እንደማያስፈልግ፥ አሊያም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አካል እንደ ሆነ ይገምታሉ። ስለ ሆነም ለማዳን ሥራው እግዚአብሔርን ማፍቀሩ አይከሰትም፤ ከዚህም የተነሣ አማኙ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት አይመራም። እንዲህ አይደለም! ኃጢአቱ ይቅር ስለ ተባለለት፥ ክርስቲያን ራሱን ሰጥቶ በምስጋና ይመላለሳል። እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ዳግም ኅብረት ለማድረግ በመቻሉና በደኅንነቱም ፍሬ ይደሰታል። ይህም አለ ጥርጥር ቅድስና ነው፡-

«ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» (ዕብራውያን 12፡14)።

ምንጩን ሳይጠቅሱ ሚስተር ጁማል ከሰርየት የተነሣ አማኙ «እንደሚድን የተረጋገጠ ስለ ሆነ እስከ ፈለገው ድረስ ኃጢአት መፈጸም ይችላል» በማለት ዶክተር ማርቲን ሉተር እንደ ተናገሩ ይገልጻሉ። ይህ ዐረፍተ ነገር

ከሌላው የሉተር ትምህርትም ሆነ ከሥራው ጋር የማይዛመድ ስለ ሆነ፥ አንቀበለውም። ይህን ዐረፍተ ነገር ማርቲን ሉተር ተናግሮታል ከተባለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የማይስማማ ስለ ሆነ፥ ከተለየ ዓውድ የቀረበ ነው ማለት ነው። በሚስተር ጄ.ማል አስተያየት የዚህ ትምህርት ውጤት ለሚከተለው ነገር መንስኤ ነው:-

> «የአውሮፓና አሜሪካ ክርስቲያን ክፍለ ዓለማት ለሚዋዥበት የሞራል ውድቀትና የግብረ-ገብነት መታጣት።»

እኛ ስለ ክርስቲያን ክፍለ ዓለም ወይም ክርስቲያን ኅብረተሰብ የምናውቀው የለንም። የተሳሳተው አመለካከት የሚመነጨው ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ ከማሰቡ ላይ ነው። ላይ ላዩን የሚመለከትም ሰው ከላይ እንደ ተጠቀሰው ወዳለ መደምደሚያ ይደርስ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይህ እውነት እንዳልሆነ አጥብቆ ይናገራል:-

> «ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ፥ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው» (ራእይ 21፡8)።

> «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩስት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቍጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ» (ገላትያ 5፡19-24)።

የዳንነው ከአንድ ነገር እና ለአንድ ነገር ስለ ሆነ፥ ይህን ከላይ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቸል ማለት ስለ ስርየት የተሳሳተ ነገር ማቅረብ



ማለት ነው። ስለ ሆነም «ከአንግዲህ ሕግን መከተል አያስፈልጋቸውም» ብሎ መደምደሙ ስሕተት ነው።

ክርስቲያኖች ከሕግ በታች አለመሆናቸው እውነት ነው።

> «በእውቀት አይቅኑ እንጂ (አይሁዶች) ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና። ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና» (ሮሜ 10፡2-5)።

> «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» (ገላትያ 2፡16)።

> ሰውን ጻድቅ ለማድረግ የሚችል ሕግ በዓለም ላይ የለም። ሕግ ትክክለኛ ወይም ስሕተት የሆነው የትኛው እንደ ሆነ ያሳያል እንጂ፥ ሰውን ትክክል የማድረግ ብቃት የለውም። ፍርድ የሚሰጥበት መመዘኛ ብቻ ነው።

> «በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና። በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና» (ገላትያ 5፡4-6)።

> «እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት። እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ:- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።

«ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው። ሕግም ከእምነት አይደለም ነገር ግን፡- የሚያደርገው ይኖርበታል ተብሏል። በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማንዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።

«ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። የሰው ስንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን ማንም አይንቅም ወይም አይጨምርበትም። ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፡- ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፡- ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ። ይህንም እላለሁ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርስም። ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም፤ በተስፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ስጥቶአል።

«እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ። መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።

«እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም። ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተስጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።

«እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ እምነት ግን መጥቶአልና



ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም። በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና» (ገላትያ 3፡6-26)።

ዳሩ ግን ይህ ማለት አማኞች እንደ ፈለጋቸው ሥርዓት በሌለው አኳኋን ይኖራሉ ማለት አይደለም።

«የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም። ወይስ ጌታን እናስቀናውን? እኛስ ከእርሱ ይልቅ እንበረታለንን?

«ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ» (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡21-24)።

ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔርን እንዲወዱና እርስ በርሳቸውም እንዲዋደዱ በደንብ አስተምሮአቸዋል።

«ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐንስ 14፡15)።

«እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ» (ዮሐንስ 13፡34)። «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» (ዮሐንስ 14፡23)።

በዚህም የብሉይ ኪዳን ትእዛዛት ሁሉ ተፈጽመዋል፡-

«ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ። ከእነርሱም አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው፡- መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸዪቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ

ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል» (ማቴዎስ 22፡34-40)።

ስርየትን በተመለከተ ተቺዎች የሚከተለውን ጥያቄ ይሰነዝራሉ፡-

«ከእርሱ ጋር ሲወዳደሩ ዋጋ ለሌላቸው፥ ኃጢአተኛና ክስማና ለሆኑት ሰዎች ብሎ ሰማያዊው አምላክ ራሱን ሰውቷል ብለን እንዴት ለማመን እንችላለን? የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ ከእስተውሎት የተቃረነና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነው።»

የተፈጥሮ ሕግ እዚህ ውስጥ እንዴት እንደሚገባ አይታየንም (ለምሳሌ ስለ እናቶች የመሥዋዕትነት ፍቅር አስብ)፤ ዳሩ ግን ምናልባት ግንዛቤአችን የተሟላ ላይሆን ቢችልም እንኳን፥ አንዳንዶቻችን ፍቅር ምን እንደ ሆነ ስመረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፡8)። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ራሱን ስለ ገለጸና በቃሉም ራሱን ስለ አሰረ፥ ሰማያዊው አምላክ እንደ ቃሉ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ መስጠቱን ለማመን እንችላለን። ይህም ዋጋ ለሌላቸው ሳይሆን፥ ለወደዳቸው ሰዎች ነው። ፍቅር ካለ ዋጋ-ቢስነት ጓዙን ጠቅልሎ ይወጣል። በሰብአዊ ደረጃ እንኳ አንድ «ዋጋ የሌለው» ሰው የፍቅር ተቀባይ ከሆነና ለዚያም ምላሹን ለመስጠት ከቻለ፥ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሰው እንደሚሆን ልብ በል። በእርግጥ ይህ አሳብ ከ«አስተውሎት» ጋር ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች፡-

«ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም መላት ደረሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌሶን 3፡19)

የሚል ማበረታቻ ተሰጥቷቸዋል።

በቃሉ ውስጥ ራሱን ስለ ሰጠና ልንደገፍበትም ስለምንችል፥ የሰማዩ አባታችንን ለማመን እንችላለን።

«ስለዚህም እግዚአብሔር፥ የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለ ፈቀደ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር (በተስፋ ቃልና በመሐላ)



... ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ፥ በመሐላ በመካከል ገባ» (ዕብራውያን 6፡17-18)።

ሌላው ከሃያሲያኖቻችን የሚቀርብብን ነቀፋ በክርስቶስ ያመኑት ሰዎች እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ስለሚሞቱ፥ ስርየት ምንም ዋጋ የለውም የሚል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ ከእግዚአብሔር ጋር የታረቀ ሰው ከዕርቁ የተነሣ በሥጋ እንደማይሞት አልተነገረንም። ይልቁንም፡-

«ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ስውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈላችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ስውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል» (ሮሜ 8፡10-11)። (ይህ በመንፈሳዊ ገጽታው አሁንም እውን ሲሆን የአማኙንም ትንሣኤ ይመለከታል።)

በሌላ ምንባብ ውስጥ ደግሞ የሚከተለውን እናነባለን፡-

«በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን» (ኤፌሶን 2፡5)።

የስርየት ዋጋ ሥጋዊ ላይሆን መንፈሳዊ ነው። ምንም እንኳ በሥጋ ብንሞትም፥ እንደ ሌላው ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ በመጨረሻው ቀን ደግሞ እንነሣለን። ዳሩ ግን ፍርድና ኩነኔ አያጋጥመንም፤ ይህ በኢየሱስ ላይ አስቀድሞ ተፈጽሞአል።

ሙስሊሞች ክርስቶስ ሕይወቱን በፈቃዱ ቤዛ አድርጎ አልሰጠም ባዮች ናቸው፡-

«በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፡- አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» (ማቴዎስ 26፡39)።

አሁንም ሃያሲያኖቻችን ዓውደ ንባቡን ቸል ይላሉ። ከመያዙ ትንሽ ቀደም ብሎ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ሲጸልይ ነበር። ከላይ የተጠቀሱት ቃላትም የጸሎቱ ክፍሎች ነበሩ። እንዲሁም የሚከተለውን ብሏል፡-

«ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች።»

ይሁን እንጂ ለጸሎቱ ማሠሪያ ያበጀው፡-

«ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን»

በማለት ነበር።

ሌላው የወንጌል ዝክር ስለ ክርስቶስ የሚከተለውን ይዘግባል፡-

«በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ» (ሉቃስ 22፡44)።

የሕክምና ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ክርስቶስ በሰይጣን ከመፈተኑ የተነሣ በጌቴሴማኒ ወደ ሞት አዝምሞ እንደ ነበር («እስከ ሞት ድረስ እጅግ እንደ አዘነ») እንመለከታለን። ይህም አብዝቶ በማይከሰተውና በሕክምና መረጃ መሠረት በከፍተኛ ሥጋት ወይም ፍርሃት ላቢያ ወደ ሞት በሚመራ በደም ላብ የተንጸባረቀ ነው። ከፊቱ የተደቀነው ነገር «መለስተኛ ቅጣት» (ኤ.ኤስ.ኬ. ጁማል) እንዳልሆነና ዳሩ ግን እጅግ የከፋ ሥጋዊ ሥቃይ እንደ ሆነ ልብ ማለት አለብን። ክርስቶስን በተመለከተ ግን ያልረከሰውና ቅዱስ የሆነው እርሱ በዓለሙ ሁሉ ኃጢአት መቆሸሹ መንፈሳዊ ሥቃዩን ከዚህም የበለጠ ያደርገዋል።

በዕብራውያን 5፡7 የተጠቀሱትን አንዳንድ መግለጫዎች ማንበቡ ጠቃሚ ነው፡-

«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር (በጌቴሴማኒ) ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት» (ዕብራውያን 5፡7)።

ይህ ወደ መስቀሉ የሚያመለክት ከሆነ እልተሰማለትም፤ እዚያው ላይ ሞቷልና። ስለዚህ የ«ጽዋ ማለፍ» ከመስቀሉ ሞት ነጻ ለመሆን የተደረገ ጸሎት ሳይሆን፥ ይልቁንም ወደ መስቀሉ እንዳይሄድ ከሚያደናቅፈው ሞት ለማምለጥ የቀረበ ጸሎት እንደ ሆነ አድርገን መደምደም አለብን።

ጻድቅና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር እንዴት ይቅር ባይና መሐሪ ሊሆን ይችላል?



ለሚለው ትልቅ ጥያቄ እስልምና የማያገኘውን መፍትሔ ነው የስርየት ሥራ ያቀረበው። ኃጢአትን በመቅጣት ጽድቁን ሲያሳይ፥ ቅጣቱን ራሱ በመቀበል ምሕረቱን ይገልጻል። ከዚህ በስተቀር ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር መሐሪም የሚሆንበት መንገድ የለም። ይህን ነጥብ ከታሪክ ውስጥ የተወሰደው ከንዋኔ በይበልጥ ያብራራው ይሆናልና እነሆ፡-

ሳሙኤል ከ200 ዓመታት በፊት የነበረ የካውካስያን መስፍን ነበር። ሕዝቡ ጎረቤታቸው ከሆነችው ከቱርክ ጋር በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ነበሩ። አንድ ጊዜ የቱርክን ከተማ በወታደሮቹ ከበበ። እናቱም እንደ ተለመደው ከእርሱ ጋር በካምፑ ውስጥ ነበረች። አንድ ምሽት ድንገተኛ የሆነ ጥቃት ለማድረግ ዐቀደ። ዳሩ ግን ጠላት ነቅቶ ይጠብቀው ነበር። ምስጢራዊ ዕቅዶቹም ከሸፉ። ድሉም ታጣ። ሳሙኤልም ወሬ አቀባዩ ከተገኘ በመቶ የጅራፍ ግርፋቶች እንደሚቀጣ በቁጣ አስታወቀ። አሁንም በትልቅ ምሥጢር ሌላ ድንገተኛ ጥቃት ታቀደ። ውጤቱ ግን ያው ነበር። ዳሩ ግን ወሬ አቀባዩ ታወቀ፤ እርሷም የሳሙኤል እናት ነበረች።

ለሦስት ቀናትና ሌሊት ራሱን በድንኳን ውስጥ ሸሸገ። ምን ያድርግ? እናቱን ቢያተርፍ፥ ሁሉም ሰው ትክክል እንዳላደረገ ይናገራል። ቢቀጣት ደግሞ ሁሉም «ሳሙኤልን እዩት! ለእናቱ እንኳ ርኅራኄ የለውም» ማለታቸው አይቀርም። በመጨረሻም ከድንኳኑ ብቅ አለ። በናፍቆት ይጠባበቀው የነበረ ጦር ሠራዊቱም ሰብሰብ አለ። ኮስተር ብሎ ለሕዝቡ እየተናገረ፡- «ከወሬ ቀብብሎሹ የተነሣ ሁለት ድሎችን አጥተናል። ሰዎቻችንም ተገድለውብናል። ነገሩን የምናቃልልባቸው መንገዶች የሉም። ጥፋቱ ስለ ተፈጸመ፥ አጥፊው ግለሰብ በሕጉ መሠረት በመቶ ጅራፍ መቀጣት አለበት! ጽድቅና ፍርድ መከበር አለባቸው» አለ።

እናቱም ወደ መግረፊያው ከበብ ተወሰደች። ፊቷ ገርጥቶ በፍርሃት ትንቀጠቀጥ ነበር። ገራፊው ጅራፉን አነሣ፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ጅራፍ ከማረፉ በፊት ሳሙኤል ጮኸ፡- «ቆየኝ! እርሷ እናቴ ነች። እኔም ከደምዋና ከሥጋዋ ነኝ። እኔ ለእርሷ ቅጣቱን እቀበልላታለሁ» አለ። ወደ ከበቡ በመግባት ልብሱን አውልቆ፡- «ገራፊ ሆይ፥ ከመጨረሻው ጥፋተኛ ባነሰ ሁኔታ ለመግረፍ አታስብ። ኃላፊነትህን ተወጣ። በል ቀጥል!» አለ። ራሱን ሰቶ እስኪወድቅ ድረስ ግርፋት በግርፋት ላይ ቀጠለ። ከተጠበቀው በላይ ግን ሕይወቱ ተረፈ። ይህ ክስተት ምናልባትም በታሪክ ከተጠቀሱት

ሁሉ በላይ ከኢየሱስ ሁኔታ ጋር ይዛመዳል። እርሱ ሥጋን የለበሰ አምላክ ነበር። ጽድቅ ፍርድም መፍረድ ነበረበት። ነገር ግን በፍጹም ፍቅሩ የእኛን (የእኔን፥ ያንተን) ኃጢአት በራሱ ላይ በማድረግ፥ የዚህ ውጤት የሆነውን ሥቃይ በመስቀል ላይ ተሠቃየ። ይህም ከፋና ጭካኔ የተሞላበት ሥጋዊ ሥቃይ ብቻ ሳይሆን፥ ይልቁንም እጅግ ንጹሕና ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር ራሱ የኃጢአታችንን አስቀያሚ ቆሻሻ በራሱ ላይ ማድረጉ እንደ ሆነ እናውቃለን።

ጽድቅና ፍቅር በኢየሱስ መስቀል ላይ ተገናኙ።

> «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን (በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የተሠራውን) አይቈጥርባቸውም ነበር» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡19)።

ይህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሆኗል። ይህ የኃጢአት መሥዋዕት ለሰዎች ሁሉ በሁሉም ጊዜ ብቁ ነው። ይህ ለእኛ የማይገባን የእግዚአብሔር ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ይሁንና ስጦታው የእኔ ሊሆን የሚችለው ስቀበለውና ስጠብቀው ብቻ ነው።

አንድ ቀራጭ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የሠራውን ትልቅ ሐውልት፥ ከዚያ በኋላ በወረቀት ላይ መልሶ ለማስፈር ቢሞክር፥ ከባለ ሦስት-ደረጃ ቅርጽ (ወርድ፥ ስፋት፥ ርዝመት) ወደ ሁለት-ደረጃ ቅርጽ (ስፋትና ርዝመት) መቀየር አለበት። እስኪ ሰውን በተፈጥሮአዊ ችሎታው፥ ሁለት-ደረጃዎችን ብቻ መረዳት ከሚችልና ለእርሱ የወርድ ደረጃ ሊገባው የሚችለው በመገለጥ ብቻ ከሆነ ፍጥረት ጋር እናመሳስለው። ለሰው ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንገዶቹ ከሰው የአመለካከት አንጻር ማብራራት ስንሞክር፥ ሁልጊዜም ከተሳሳተ መንደርደሪያ እንጀምራለን። በተለይም ሃያስያኑ የኃጢአተኛን ቅጣት እንደ እርማትና እንደ አድሳት መንገድ አድርገው ሲጠቅሱት የሚፈጸመው ነገር ምንድነው? ስለ ኃጢአት ምንነት ያለውን መለኮታዊ አመለካከት አልተረዱም። ይህን ወደ ጎን የምንተው ከሆነ፥ የሃይማኖት ሥነ- ሥርዓት መፈጸሙ «ለጥቃቅን ስሕተቶቻችን» ማካካሻ ይሆናሉ ወደሚለው ማጠቃለያ የግድ መድረስ አለብን። ይሁን እንጂ ኃጢአት በሁሉም የተግባራዊ ሕይወት ገጽታዎች በራስ ፈቃድ መመላለስ ሲሆን፥ በሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ኃላፊነቶች የማካካስ ነገር



መሳምት ብቻ ነው። ኃጢአት በማስተዋል እና ባለማስተዋል በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዓመፅ መሆኑ፥ ኃጢአተኛውን ሙሉ በሙሉና ለዘላለም ከእግዚአብሔር ይለየዋል። ያለፈውን ኃጢአት በተመለከተ የሚደረግ ማንኛውም እርማት ቢሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ካልመጣ በቀር የማይታሰብ ነው። ለሰው አስፈላጊ የሆነው ነገር ከአድሳት የጠለቀ ነው። የስውየው ሙሉ ተፈጥሮ መለወጥ አለበት፡-

> « እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ 12፥1-2)።

እኛ በራሳችን ይህን መለወጥ ልናመጣው አንችልም፥ ወይም በሃይማኖታዊ ተግባሮች ሊመጣ አይችልም። ይህ በጸጋው የሆነ የእግዚአብሔር የማዳን ውጤት ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ መመልከት የሚያሻን አንድ የመጨረሻ ነጥብ አለ። የእግዚአብሔር ቅጣት ዓላማ ኃጢአተኛውን ለማረም ከሆነ፥ ኃጢአተኞች ይህን ቅጣት በሚቀበሉበት በፍርዱ ቀን ምን ፋይዳ ሊኖረው ይችላል? የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ ብንተውና በስፍራውም ሃይማኖትን ብንተካ፥ ራሳችንን በማታለል ከእግዚአብሔር መለየትን እንመርጣለን። በዚህ ዓይነት ገሃነመ እሳት ቅጣት ሳይሆን፥ የራሳችን ምርጫ ነው። ከእርሱ ጋር የነበረውን ግንኙነት መታጣት መልሶ ለመመሥረት በእግዚአብሔር የተሰጠ ብቸኛ አማራጭ ስርየት ነው። ይህ ሁሉንም የሕይወታችን ገጽታ የሚመለከትና የሕይወታችንን መለወጥና መቀየርን የሚያስከትል ነው። ስው በራሱ ችሎታ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደሚችል የተያዘው ምናብ፥ ቀደም ብለን እንደ ደረስንበት ብቸኛውና ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው። ይህ ኃጢአት ሲታወቅና ንስሐ ሊገባበት አዲስ ሕይወት ይጀምራል። ብዙዎች ግን እጅግ ግራ ስለ ተጋቡና፥ በዚህ ጽንሰ አሳብ ላይ እስከ መጨረሻው ድረስ ለማሰብ እንኳ ስለሚቸገሩ፥ ኢየሱስንና ስርየቱን አይቀበሉም።

«ይህ የስርየት አሳብ የተጠነሰሰው ከጳውሎስ የፈጠራ ብልሃት የተነሣ» እንደ ሆነ ክርስቲያኑ ከሚስተር ጁማል በመደነቅ የሚሰማው ነገር ነው። ኢየሱስ በእርግጥ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ፥ ነገር ግን የሞተ እንደ መስለና ስለዚህም እንደ በድን በመቃብር ውስጥ እንደ ተደረገ ይተርካል። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በሱረቱ 4፡ 157

«አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም»

ከሚለው ከቁርዓን ጋርም በቀጥታ ይቃረናል። የሚስተር ጁማል ዐረፍተ ነገር በሚርዛ ጉላም አሕመድ የተዘጋጀው የአሕመዳውያን እምነት ነው።

የእርሱ አመለካከቶች በሱኒ ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የተነፈጋቸው ቢሆኑም፥ ብዙውን ጊዜ ለገዛ ጥቅማቸው ሲሉ የሚያስራጯቸው ናቸው። ከዚያም ዘገባው ስለ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡-

> «ሕክምና ከተደረገላቸው በኋላ ቁስሎቹ ዳኑ። በዚህም ጊዜ ከመቃብሩ በመውጣት በምስጢር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተገናኘ። በሮም መንግሥት የሞት ፍርድ የተላለፈበት ስለ ሆነ፥ በሕይወት እንዳለ ቢታወቅ አደገኛ ይሆን ነበር። ማንነቱ ታውቆ ቢሆን ኖሮ፥ እንደገና ይታሠርና ለሁለተኛ ጊዜ ይፈረድበት ነበር። ደቀ መዛሙርቱስ ክርስቶስ እንዳልሞተና ዳሩ ግን ሕያው እንደ ሆነ እንዴት ይገልጻሉ? በሌላ በኩል አይሁዶች ኢየሱስ እንደ ሞተ በደስታ አውጀዋል። ምክንያቱም እርሱ የተረገመ አስመሳይ ሰው ነበርና ነው። ‹በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር የተረገመ ነውና› ይላል ዘዳግም 21፡23።»

ይህ ግምት ስለ ኢየሱስ ሞት ብቸኛ ዝርዝር ለሆነው ለአዲስ ኪዳን የዓይን ምስክሮች ዘገባ ሙሉ ለሙሉ እንግዳ ነው።

> «አይሁዳውያን ኢየሱስን ለመስቀል የፈለጉበት ዓላማ ሐሰተኛ መሆኑን ለማሳየትና በዚያውም የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት ለማረጋገጥ ነበር። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም ምን እንደሚያደርጉ ወይም እንደሚናገሩ አያውቁም ነበር። በማመንታት ላይ ነበሩ። በመስቀል ላይ እንደ ሞተ ማመኑ «በእግዚአብሔር የተረገመ ነው» የሚለውን እምነት ያጠናክረዋል። በሕይወት እንዳለ ማወጁ ደግሞ



> የባሰ አደገኛ ነበር . . . እዚህ ላይ ነበር የጳውሎስ የፈጠራ ችሎታ መሥራት የጀመረውና ደቀ መዛሙርቱ ያልተቃወሙትን የብልሃት ዕቅድ የወጠነው። ያልተቃወሙትም ከነበሩበት ቀውጢ ሁኔታ የሚወጡበት ብቸኛው መንገድ ይኸው መስሎ ስለ ታያቸው ነው። ጳውሎስ ኢየሱስ ያለ ጥርጥር የተረገመ ሞት ሞቷል፥ ዳሩ ግን እርሱ ራሱ ንጹሕ ሆኖ ሳለ የሰዎችን የኃጢአት መርገም በትከሻው ላይ ተሸከመ፤ ይህ ዝናውን የሚያጎድፍበት አይደለም ይልቁንም እጅግ የከበረ ሥራ ነው የሚል ጽንስ-አሳብ አቀረበ። ስለ ሆነም ክርስቲያኖች ዛሬ ቢያንስ ለአይሁዶች የሚሰጡት መልስ አላቸው። ይህ ጽንስ-አሳብ በመጀመሪያ ለአይሁዶች ምላሽ እንዲሆን የተዘጋጀ ይሁን እንጂ ቀስ በቀስ ዛሬ በክርስቲያን ሚስዮናውያን በመሰበክ ላይ ወዳለው የስርየት ትምህርት አድጓል።»

ስለ ሚስተር ጁማል የተለየ ዓይነት መልእክት ምንጮች በበለጠ ለማወቅ እንሻለን። በተጨማሪም በፕሮፌሰር ዶክተር አርኖልድ ሜየር ከተጻፈው «ኢየሱስ ወይስ ጳውሎስ» ከተሰኘው መጽሐፍ ይጠቅሳል፤ የሚከተለውንም ይነግረናል፡-

> «ፕሮፌሰሩ የኢየሱስ አምላክነትና ስርየት ምንጫቸው ከጳውሎስ ዘንድ የሆነ ጭፍን አምነቶች እንደ ሆኑ በማያጠራጥር መንገድ ያረጋግጣል። «ኢየሱስና ሐዋርያቱ» ይላሉ ፕሮፌሰሩ «ስለ እነዚህ ትምህርቶች የሚያውቁት አልነበራቸውም።» ሚያንደር «የቤተ ክርስቲያንና የክርስትና ሃይማኖት ታሪክ» በተሰኘው መጽሐፉ፥ «የስርየት ትምህርት እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ዛሬ በክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እንደሚታመነው ባለው መልኩ ግልጽና ጉልህ ሆኖ አልተቀናበረም ነበር» ብሏል።

> «እንዲሁም በታልሙድም ሆነ በቶራ ውስጥ ስለ ስርየት የተጠቀሰ ምንም ነገር አናገኝም።»

የእነዚህን አባባሎች መሠረተ ቢስነት ቀጥለን ለማሳየት እንወዳለን።

1. እንደ ክርስቶስ ሕይወት በሚገባ በመረጃ የተደገፈ አንድም የጥንታዊ ክስተት የለም። የታሪክ ሰዎች የአዲስ ኪዳንን የመረጃ ተአማኒነት

የሚጠረጥሩበት ምንም ምክንያት የላቸውም (ከገጽ 145 ጀምሮ ተመልከት።)

2. ስለ ስቅለቱ ከውስጣዊ መረጃ በተጨማሪ በሌሎችም የዘመኑ ጽሑፎች ውጫዊ መረጃ አለ (ከላይ እንደተመለከተው)።

3. ከላይ የተጠቀሱትን መግለጫዎች የጻፈው ሰው ምሁር ብቻ መሆኑን ስለምናውቅ ሐቀኝነቱን ለመጠራጠር እንገደዳለን። ጳውሎስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማበር እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ለማቀናበር ሴራ አድርጓል ሲል ለጠቀሰው ምላሽ ለመስጠት፥ ጳውሎስ እስከ ተለወጠበት እስከ 36 ዓ.ም. አካባቢ ወይም ክርስቶስ ከሞተ ከ6 ዓመታት በኋላ የክርስቲያኖችን ቤተ ክርስቲያን ያሳድድ እንደ ነበር እንመለከታለን። ከዚያም በኋላ ብቻውን በአረቢያ አገር ውስጥ ለሦስት ዓመታት ተቀመጠ። ስለ ሆነም በትንሣኤ፥ ዕርገትና ጳውሎስ የማስተማር አገልግሎቱን በአንጾኪያ (በበርናባስ ተጠርቶ) በጀመረበት ጊዜ መካከል የአሥር ዓመታት ልዩነት ነበር። በመሆኑም «የብልሃት ዕቅዱ» ከታሪክ አንጻር ተቀባይነት አይኖረውም።

4. ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ እኛ እርግማን በመቀበል «በእግዚአብሔር የተረገመ» ሆነ። «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላትያ 3፡13)።
የዓለሙ ኃጢአትና የኃጢአት መርገም በእርሱ ላይ ነበረ።

5. ሚስተር ጁማል ፕሮፌሰሮችንና የትርጓሜ አዘጋጆችን ሲመርጡ፥ በክርስቲያኖች ዘንድ ምንም ዋጋ የማይሰጣቸውንና ትምህርቶቻቸውንም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የማይመሠርቱትን ባለ ለዘብተኛ አቋሞቹን ነው። «እንደ የኢየሱስ አምላክነትና ስርየት ዓይነቶቹ ጭፍን እምነቶች ማረጋገጫዎች ምንጫቸው ጳውሎስ ነው» የሚለው ብሒል ፍጹም ትርጉም የማይሰጥ ነገር ነው። ይበልጥ ትርጉም የማይሰጠው ደግሞ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ስለ እነዚህ ትምህርቶች የሚያውቁት አልነበራቸውም የተባለው ነው። «ስርየት» የተባለው ቃል ከክርስቶስ ዘመን በፊት ወደ ሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ በቆየው ብሉይ ኪዳን ውስጥ 79 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ተጽፎአል።



እንደ አጋጣሚ «ስርየት» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የተጻፈው።
«አሁን መታረቁን (ስርየቱን) ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን» (ሮሜ 5፡11)።

የዘሌዋውያን መጽሐፍ (1500 ዓ.ዓ) 16ኛው ምዕራፍ በሙሉ ለ«ስርየት ቀን» የተሰጠ ሲሆን በ17፡11 ደግሞ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡-

«የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።»

የእስልምና ባህል ቁርባን የማቅረቡ ልማድ መሐመድ ከመዲና አይሁዶች ጋር ከሂጅራው በኋላ በመጀመሪያው ዓመት የፈጸመው ከዚህ ከስርየት ቀን እንደሚጀምር ይናገራል።

የዘጸአትና የዘሌዋውያን መጻሕፍት በተለይ በስርየት ዘገባዎችና ትምህርቶች ላይ የሚያተኩሩና በእግዚአብሔር ሕግ ላይ መተላለፍን ባደረገው አማኝ ምትክ በሚሆነው መሥዋዕት አስፈላጊነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ተላላፊው መሥዋዕቱን ወይም የኃጢአቱን ማስተስረያ ወደ መሠዊያው በማቅረብና በመሥዋዕቱ ራስ ላይ እጁን በመጫን መናዘዝ ነበረበት፥ ከዚያም መሥዋዕቱ ይታረዳል። ይህም የተላላፊው ጥፋቶች በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል አስከፊ እንደ ሆኑና ለዚሁም የሚገባው ቅጣት ብቻ መሆኑን ያሳየዋል። በእርግጥ «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነው» (ዕብራውያን 9፡9-19፤ 10፡1-4)። ዳሩ ግን እነዚህ መሥዋዕቶች በኢየሱስ ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት አስቀድመው በጥላነት አመልክተዋል።

የስርየት ትምህርት በማንኛውም ጊዜ በክርስቶስ በፍጹም አልተሰበከም ተብሎ የሚነገረውም እውነት አይደለም። የዚህ መንስኤው የሃያስያኑ መሐይምነት ይሁን ወይንም ቅጥፈት እርግጠኞች አይደለንም። ማቴዎስ 20፡28ን እንጠቅሳለን፡-

«እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።»

«ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» (ማቴዎስ 26፡28)።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3፡16)። (እንዲሁም «የእግዚአብሔር ልጅ» በሚለው ርዕስ ሥር ያለውን ማስታወሻ ተመልከት ገጽ 139።)

«ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ... እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» (ዮሐንስ 6፡51)።

«መልካም እረኛ ነፍሱንም ስለ በጎቹ ያኖራል ... ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ ... እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም» (ዮሐንስ 10፡11፥ 15 ና 18)።

ወደ ብሉይ ኪዳን በመመለስ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የኢሳይያስ 53ን ትንቢት እናገኛለን፡-

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል ... እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን ... እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ... ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመታ ... እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ ... የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።»

በመጨረሻም ከሃያሲያኑ ዘንድ ስርየትን በተመለከተ ከተሰነዘሩት የመሟገቻ ጥያቄዎች ሁለቱን ለመመለስ እንወዳለን፡- «የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለክርስቲያኖች ያደረገላቸው ነገር በትክክል ምንድነው?»

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

«በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን



ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ» (ገላትያ 3፡13-14)።

«አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና ... ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ...በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» (ኤፌሶን 2፡13-16) (ጥሉ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መሆኑ ነው)።

«ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ ... የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል» (ቲቶ 2፡11-14)።

ሌላው ጥያቄ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

«መሥዋዕቱ በክርስቶስ በሚያምኑና ሥጋ ወደሙን በሚካፈሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለኃጢአት የጥላቻ ስሜት አሳድሯል ወይስ ክፋትን ለማድረግ ያለውን ዝንባሌ ገድሏል?»

በማጠንከር የምንሰጠው ምላሻችን መቼም አዎን ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ከዳነ በኋላ በኃጢአት ተዘፍቆ አይኖርም። እውነተኛ ክርስቲያን ማለቱ ነው (ከገጽ 193 ጀምሮ)። በሕይወታቸው ይህ የማይሆንባቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ግብዞች በማለት ይጠራቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም አዲስ ኪዳን በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ተግሣጾች አሉት፡-

«ከኃጢአት እርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ተገዛችሁ» «እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ»

> «ኃጢአት አይገዛችሁምና» «ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?» (ሮሜ 6)።

> «በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም» (ሮሜ 8፡8-9)።

> «ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ» (ገላትያ 5፡13)።

> «ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር» (ፊልጵስዩስ 2፡3)።

> «እውነተኛ ... ጭምትነት ... ጽድቅ ... ንጹሕ ... ፍቅር ... መልካም ወሬ ... በጎነት ... ምስጋና ... እነዚህን አስቡ» (ፊልጵስዩስ 4፡8-9)።

> «ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ... ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ... በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት» (ቈላስይስ 3፡12-14)።

ሌሎች ብዙ ክፍሎችንም መጥቀስ ይቻል ነበር።

ይህ ማለት ግን ክርስቶያኖች ኃጢአት አልባ ናቸው ማለት አይደለም። ዳሩ ግን በጣም አናሳ የሆኑትን ሳይቀር፥ ኃጢአትን ይጠላሉ፤ በኃጢአት የተሞላ ሕይወትም አይመሩም። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ቢረቱለትም እንኳ በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፡-

> «ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1፡10)።

እንግዲህ የክርስትናን እምነት እየተከተለ የግብረ ገብነት ኑሮ ስለ ራቀውና የሞራል ውድቀት ስለ ተጫነው የምዕራቡ ዓለም ምን እንላለን? በርካታው



ሕዝብ የቤት ክርስቲያን አባልነት ካርድ እንዳለው ከመናገሩ ወይም እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ እንዳለ ከማመኑ የተሻለ ነገር የለውም። ይህ የክርስትና እምነት አይደለም! እነርሱን ክርስቲያኖች ብሎ መጥራት የአዲስ ኪዳን ትርጉሙን ማሳጣት ማለት ነው። ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተሰጠና በቃሉም የሚኖር ነው።

በመደምደሚያም ስርየት ማለትም የእግዚአብሔርና የሰው መታረቅ ከመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ጀምሮ መሥዋዕቱ በመስቀል ላይ እስከ ተፈጸመበት ጊዜ ድረስ የእግዚአብሔር ጥሪ በመሆን በሥራ ላይ የዋለ መሆኑን በመግለጽ ለማጠቃለል እንችላለን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያን አማኞች ሁሉ በክርስቶስ በተሰጠው ስርየት በመጠቀም የክርስትና ሕይወታቸውን መኖር ጀምረዋል። ከዚያም ይህን በር የከፈተላቸውን ክርስቶስን ያገለግላሉ፡-

> «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውንም አይቈጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17-21)።

## የኢየሱስን አምላክነትና ልጅነት በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

የኦክስፎርድ የሪፖን ሆል ኃላፊ የሆኑት ሬቨረንድ ኤች. ዲ. ኤ. ሜጀር በ1921 በኦክስፎርድ በተደረገው የሃይማኖት ጉባኤ ላይ የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡-

> «የድንግል መውለድ ታሪክ እንደሚጠቁመው በሥጋዊ መንገድ፥ ወይም ደግሞ በኒቂያን ሥነ-መለኮት እንደሚጠበቀው በረቂቅ መንገድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በወንጌላት

> ውስጥ አለመናገሩ ግልጽ ሆኖ ሊታወቅ ይገባል። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ሲል፥ የሰው ልጅ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነቱን በሚገልጽበት አኳኋን የአባትና የልጅነት እንዲሁም ግብረገባዊ ዝምድና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሁኔታና እግዚአብሔር በሚሠራባቸው በእነዚህ ግብረገባዊ መመሪያዎች ላይ ለመሥራት ችሎታ እንዳለው በሚገልጽ መንገድ ነው።»

> «በዚህ ስብሰባ ላይ በሊቀ መንበርነት የተቀመጡት፥ የካርላይል ዲን ዶክተር ራሽዳል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር አድርገው እንዲቀበሉ እንዳልፈቀደላቸው በመግለጽ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ አስደንጋጭ ዜና አስተላልፈዋል። ምሁሩ ዲን እንዳስቀመጡት፥ ኢየሱስ በሁሉም ሙሉ ለሙሉ ሰው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም» («መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወይስ የሰው ቃል?» በኤ. ኤስ. ኬ. ጁማል)።

አሁንም «ባለ ለዘብተኛ አቋሞቹ» አመለካከታቸውን እንዲገልጹ ተጠርተዋል። ቃላቸው እንዴት ነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማው?

የኢየሱስ መለኮታዊነት የሮማ የጳጳሳት፥ የዲኖች፥ የጳጳሳት ወይም የቀሳውስት አስተሳሰብ አይደለም፤ አስተሳሰባቸው በምንም ዓይነት ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና የሬቨረንድ ኤች ሜጀር እና የዶክተር ራሽዳልም በእርግጥ እንዲሁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ክርስቲያኖች መልእክቶችንና ትምህርቶችን በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይወስዳሉ እንጂ፥ አሳባዊ፥ ግላዊና ሰው እንዳሻው የሚተረጉማቸውን ነገሮች አይቀበሉም። ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና በቤተ ክርስቲያን ጭፍን እምነት መካከል ግልጽ ልዩነት ሊኖር እንደሚችል መመልከቱ አስፈላጊ እንደ ሆነ አያለሁ።

የሚያሳዝነው ሙስሊሞች «ሥላሴ»፥ «የእግዚአብሔር ልጅ» ወይም «የክርስቶስ መለኮታዊነት» የሚሉ ዓይነት ቃላት በሚሰሙበት ጊዜ በቁርዓን ውስጥ የሚገኙትን፡-

«አላህ አልወለደም፤ አልተወለደምም» (ሱረቱ 112፡3)



የሚሉት ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች በተናጠል ትውስ ይሏቸዋል። እዚህ ላይ ሥላሴን የተረዱት እግዚአብሔር፥ ማርያምና ኢየሱስን (ሱረቱ 5፡116) የሚያጠቃልልና፥ ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ሥጋዊ ውህደት አድርገው ነው። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ነው፤ መሐመድም ሥጋዊ ውህደትን በመቃወሙ ትክክል ነው። እንዲህ ዓይነቱ «ሥላሴ» በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ከትምህርት ላይ አልዋለም፤ ምናልባት ማርያም በውሸት «የእግዚአብሔር እናት» ተብላ በተጠራችበት በመካከለኞቹ ዘመናት በተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ካልሆነ በስተቀር። መጽሐፍ ቅዱስን አለማወቅ ብዙውን ጊዜ ሙስሊሙን ወደ ተዛባ መደምደሚያ እንዲደርስ ያደርገዋል።

ቁርዓን እንኳ በተለየ የአገላለጽ ዘይቤው ለክርስቶስ ልጅነቱ መንገድ ይከፍታል። መልአኩ ለማርያም እንዲህ ሲል ተናገራት፡-

> «እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ፥ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት። (በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ኾኜ፥ አመንዝራም ሳልኾን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች። አላት፡- (ነገሩ) እንደዚህሽ ነው፤ ጌታሽ፡- እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ ለሰዎችም ታምር፥ ከኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው አለ፤ (ነፋባትም)» (ሱረቱ 19፡19-21)።

> «ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፥ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ . . .» (ሱረቱ 3፡45)

በሱረቱ 19 ከኢየሱስ እናት ጋር ተዋውቀናል። «ይኼ ለእኔ ቀላል ነው» በሚለው ሐረግ እንደ ተመለከተው እግዚአብሔር የቅዱሱ ልጅ የአባት ምሳሌ ነው። ይህ በሥጋዊ ውህደት ስላለመፈጸሙ ዳሩ ግን በቅዱስ መንፈስ እንደ ሆነ እንስማማለን። የሰውን መንፈስ ከራሱ ከሰውየው ለይቶ ለማየት ስለማይቻል፥ የንጹሑ ጽንስ ተአምር ተፈጸመ፤ «ቅዱሱ ልጅ» ኢየሱስም ተወለደ።

ቁርዓን የኢየሱስ ክርስቶስን የተለየ መሆንና በምድር ላይ ከኖሩት ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የሚወዳደረው ያለመኖሩን ሐቅ በምንም ዓይነት አያናንቅም።

1. ከድንግል ተወልዷል (ሱረቱ 19፡16-35)።

2. እርሱ መሲሕ ነበር (ሱረቱ 4፡ 171)። ቁርዓን መሢሕ ምን እንደ ሆነ አያብራራም። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሙ ተቀባይነት አግኝቷል ብለን እንገምታለን። አስቀድሞ የተነገረውና ተቀባይነት ያገኘው የመሢሑ ሥራ ነፃ የማውጣትና የማዳን ተግባር ነው።

3. እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መንፈስ ነው (ሱረቱ 4፡ 171)

4. እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነበር (ሱረቱ 4፡ 171)። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት ነው (ዮሐንስ 1፡ 1-14)።

5. እንከን አልነበረበትም (በማርማዱክ ፒክታል የተተረጎመ) ወይም እርሱ ቅዱስ ነበር (በዩሱፍ አሊ የተተረጎመ) (ሱረቱ 19፡ 19)። ይህ ከማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ነቢይ በተቃራኒ የተነገረ ነው፡-
አዳም ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 2፡ 36፤ 7፡ 22-23)።

   አብርሃም ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 26፡ 82)።

   ሙሴ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 28፡ 15-16)።

   ዮናስ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 37፡ 142)።

   ዳዊት ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 38፡ 24-25)።

   መሐመድ ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 47፡ 19፤ 48፡ 1-2፤ 33፡ 36-38)።

6. በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም የተከበረ ነው (ሱረቱ 3፡ 45)።

7. በእግዚአብሔር ወደ ሰማይ ተወስዷል (ሱረቱ 4፡ 158)።

8. ለፍርድ እንደገና ወደ ዓለም ይመጣል (ሱረቱ 43፡ 61 በዩሱፍ አሊ የተተረጎመ እና ሚሽካት 4 ገጽ 78-80)።

ሌላ አመለካከት ከቁርዓን መውሰድ ይቻላል። እርሱም በትክክል እንደሚከተለው ይዘግባል፡-

> «እላንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ፤ ለርሱም አድምጡት፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት)፥ ዝምብን ፈጽሞ አይፈጥርም፤ ለርሱ (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳ፥



> (አይችሉም)፤ አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም» (ሱረቱ 22፡ 73)።

ሕይወትን ለመፍጠር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ሁላችንም እንስማማለን። እስቲ እንግዲህ በዚህ አመካኝነት ወደ ኢየሱስ እንመልከት፡-

> «እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በርሱም እተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፥ ለምጸኛንም፥ አድናለሁ፤ ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት» (ሱረቱ 3፡ 49)።

ከምንባቡ ሕይወትን እና ጤንነትን የፈጠረው (በሞቱ ሰዎችና በወፎች) ኢየሱስ እንደ ነበረ እንረዳለን። ከምንባቡ ላይ በእግዚአብሔር የመፍጠር ሥራ እንደ መሣሪያ ሆኖ እንዳላገለገለ ሳይሆን፥ ይልቁንም ራሱ ፈጣሪ እንደ ነበረ ግልጽ ነው።

በብዙ ቁጥሩ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር አንድነት የተጠቀሰው ሌላ አስደሳች አሳብ በዶክተር ኤ. ሀቅ ቀርቧል፡-

> እግዚአብሔር በራሱ ተፈጥሮም እንኳ ፍጹም አንድነት ካለው፥ የተፈጥሮውን ባሕርያት በተመለከተ ጥያቄ ይነሣል። እነዚህ ባሕርያት የእግዚአብሔርነቱ ባሕርያት አካል ናቸው፥ ወይስ ከእርሱ ውጭ ናቸው? እነዚህ በእሱነቱ ባሕርይ ውስጥ የሚጠቃለሉ ከሆኑ፥ እንግዲህ በዘጠና ዘጠኝ ደረጃዎች የሚገልጽ አንድ የእሱነቱ ባሕርይ አለን ማለት ነው (የአላህን ባሕርያት በተመለከተ)። የእግዚአብሔር ፍጹም ዘላለማዊ አንድነቱ በዚያው ውስጥ ለበርካታነቱ ስፍራ መስጠት አለበት። በሌላ በኩል፥ ደረጃዎቹ ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ውጭ ከሆኑ፥ መለኮታዊ አይሆኑም። በዚህ ረገድ ውቦቹን ስያሜዎችን ሁሉ ለአላህ መስጠቱ ተፈጣሪዎችን ከፈጣሪ ጋር ማስተካከል ይሆናል። ይህ በእስልምና እምነት መሠረት፥ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ከሁሉም የከፋ ኃጢአት ነው። ስለዚህ

በእግዚአብሔር ውስጥ በብዙ ደረጃዎች ያለ አንድ ተፈጥሮ የሚለው የመጀመሪያ አማራጭ ሊረታ ይገባዋል።

ሌላው የእግዚአብሔርን ፍጹማዊ አንድነት በተመለከተ የሙስሊም የአስተሳሰብ ችግር የሚከሰተው፥ ከራእይ ወይም ከመገለጥ ዓውድ አንጻር ነው። ቁርዓን ስለ መገለጥ የሚናገረው በሰማይ እንደ ተዘገበና መልአኩ ገብርኤል ለነቢያት እንዳመጣላቸው አድርጎ ነው። ይህ ዘገባ ወይም በሰማይ ያለው የመጀመሪያው መጽሐፍ «የመጽሐፉ እናት» (13፡39) ተብሎ ይጠራል። ይህ የሰማዩ መጽሐፍ መገለጥን ሁሉ፥ እንዲሁም የነገሮችንና የክስተቶችን ዘገባ ሁሉ ያካትታል (57፡22፤ 17፡37፤ 6፡38)። የሙስሊም ሥነ-መለኮት ራሱ፥ «ይህ መጽሐፍ በሰማይ ለዘላለም የኖረ ነው ወይስ የተፈጠረ ነው?» የሚልን አሰቸጋሪ ጥያቄ ሰንዝሯል። ቁርዓን ራሱ በዚህ ነጥብ ላይ ምንም መረጃ አይሰጥም። ይሁንና የኋለኛው አርቶዶክስ ሥነ-መለኮት ስለ መጽሐፍ እናት ዘላለማዊነት ተናግሯል። አል-ጋዛሊ ይህን የእግዚአብሔር ዋንኛ ባሕርይ አካል አድርጎ አቅርቧል።

የመጽሐፉ እናት ዘላለማዊ ከሆነች፥ እንግዲህ በእግዚአብሔር ውስጥ ወይም አጠገብ መኖር አለባት። መጽሐፏ ከእግዚአብሔር ዘንድ ካለች፥ በሁለት አማልክት ማመንን የሚያመለክቱ ሁለት ዘላለማዊ ነገሮች አሉ ማለት ነው። አል-ጋዛሊ ይህን ችግር ስለ ተገነዘበ፥ ሌላውን አማራጭ ወሰደ። ይህም መጽሐፏ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ እንዳለች አድርጎ መቀበል ነው። እዚህ ላይ ክርስትና ከአባቱ ጋር አንድ አምላክነት ባለው በእግዚአብሔር ቃል፥ ወይም ልጅ (ሱረቱ 4፡171) ላይ ያለው የክርስትና እምነት፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ካለው የተመዘገበ መጽሐፍ ያነሰ ትርጉም ይሰጠው እንደ ሆነ ሙስሊሙ ራሱ እንዲፈርድ ሊያበረታታው ይችላል። ለዝንጉነት እንደ ተጋለጡት የሰው ልጆች፥ እግዚአብሔር የራሱን መግለጫዎች መዝግቦ ማቆየት አያስፈልገውም። ዳሩግን ነገሮች ሁሉ በቃሉ ተደግፈዋል (ዕብራውያን 1፡1-3)። ይኸው ቃል ወይም የእግዚአብሔር ልጅ የፍጥረት፥ የራእይና የደኅንነት ምንጭ ነው። እርሱም በተወሰነ የታሪክ ምዕራፍ ላይ «ሥጋ ሆነ ጸጋንና



እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን› (ዮሐንስ 1፡14)።

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ብርሃን፥ አንድ ሰው ኢየሱስ ተራ ሰው ወይም ነቢይ እንደ ሆነ ሊናገር ይችላልን? እንዲህ ያሉ ባሕርያትና ምግባሮች ያሉት ነቢይ የት አለ?

ሙስሊሞች የክርስቶስ ልጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ከአማኞች ወይም ከመናፍስት «ልጅነት» ጋር የሚምታታባቸው ይመስላል። ቅዱስ ዮሐንስ የጻፈው ወንጌል በ3፡16-18 ላይ ስለ እግዚአብሔር አንድያ ልጅ፥ ወይም ብቸኛ ልጅ ይናገራል፡-

> «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።»

«አንድያ» የሚለው ቃል ከ1611 ዓ.ም. ትርጉም የተወሰደ ሲሆን፥ ትርጉሙ ዛሬ በተለየ መንገድ ነው የሚገለጸው። አንድ ሕያው የሆነ ቋንቋ ይለወጣል። በመጀመሪያዎቹ የግሪክ መዛግብት ውስጥ ቃሉ «ሞኖጀኔስ» («ሞኖ» = አንድ፥ «ጀኔስ» = ተወለደ) ነው። የማስረገዝን ድርጊት አይጠቁምም።

ከዚህ በተጨማሪ፥ ፍርድ ሁሉ ለልጁ እንደ ተሰጠ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንረዳለን፡-

> «አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና። የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው። በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ» (ዮሐንስ 5፡26-29)። («የሰው ልጅ» የሚለው ስያሜ በ500

> ዓ.ዓ. በነቢዩ ዳንኤል የተነገረ ነው (ምዕራፍ 7፡13፤ 10፡16)። ይህ ማን ሊሆን እንደሚችል ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለም።)

ክርስቶስ በአይሁድ የመሰደዱ እውነተኛ ምክንያት ይኸው ነው፡-

> «እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፡- እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር» (ዮሐንስ 5፡18)።

ሙስሊሞችንና ሂዩማኒስቶችን (የሰብአዊ ፍጡርን ክቡርነት የሚያጎላ ፍልስፍና ተከታዮች) የክርስቶስን አምላክነት እንዲክዱ በተደጋጋሚ የቀሰቀሱአቸው ምክንያቶች አሉ። ክርስቶስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ፡-

> «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» (ማቴዎስ 4፡10)

ብሎ እንደ መለሰ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይጠቅሳሉ። ይህ ዐረፍተ ነገር የክርስቶስን መለኮታዊ አለመሆን ያረጋግጣል ተብሎ ተገምቷል። ግና ክርስቶስ ሰይጣንን ማምለኩን አጥብቆ ስለ ተቃወመ ነጥባቸው የቱ ላይ እንደ ሆነ ለማየት ይሳነናል።

ከዚያም ኢየሱስ ለሚመረምረው አለቃ የሰጠው ምላሽ በሉቃስ 18፡19 ላይ እንደሚከተለው ተጽፎአል፡-

> «ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።»

በመጀመሪያ ዕይታ የተጠቀሱት ምንባቦች ኢየሱስ ክብርንና ማዕረግን ያልፈለገው የማይገቡት በመሆናቸው እንደ ሆነ ያስመስላሉ። ዳሩ በእርግጥ እውነቱ እንደዚህ ነውን?

> «የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ።»

ይህንንም ያደረገው ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሆኖ ሳለ ነው (ፊልጵስዩስ 2፡6-7)። ይሁንና ሁኔታውን መመልከት የሚገባን በሚከተለው ዓውድ ሊሆን ይገባዋል። ጠያቂው ኢየሱስን «ቸር መምህር» (አስተማሪ፥ ሺኺ)



ብሎታል። ነገሩን ወደ ሌላ አቅጣጫ በማመልከት ኢየሱስ፡- «መምህር ቸር አይደለም። ቸር እግዚአብሔር ብቻ ነው። ቸር ብለህ እኔን መጥራትህ ማለፊያ ቢሆንም እንኳ፥ እኔ ከመምህር በላይ ነኝ» ማለቱ ነበር።

ሌላም በኢየሱስ ላይ የተደረገ ውስንነት አለ፡-

> «አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም ... እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» (ዮሐንስ 5፡19፥30)።

በግልጽ የሚታየው የክርስቶስ ሁሉን አለማወቅ ብዙ ሃያሲያንን ወደ አንድ መደምደሚያ መርቷቸዋል። እንዲህም ሲሉ ይጠቅሳሉ፡-

> «ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም» (ማቴዎስ 24፡36)።

> «(እግዚአብሔር) ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና። ነገር ግን፡- ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡27-28)።

እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ከሠፈው የቅዱሳት መጻሕፍት ዐውድ አንጻር ቢታዩ፥ ሁሉ ነገር ተገቢ ቦታውን ይይዛል። ክርስቶስ በሰብአዊ አካል በነበረ ጊዜ ባመዛኙ በሰው ላለው ዓይነት ውስንነት ተዳርጓል። ለአብነትም፡-

በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ መወሰን ነበረበት። እንደ ሰዎች ስሜት፥ የእውቀትም ውስንነት ነበረው። ምንም እንኳ ከሰብአዊ ችሎታ በላይ የሆኑ ተአምራት ቢያደርግም፥ ሙሉ ለሙሉ ሰው ነበር።

እንግዲህ ክርስቶስን በተመለከተ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው ባሕርይ ተመሳሳይ ከሚመስሉት ከሁለቱ አባቦች በስፋት እንደሚለይ እንመለከታለን። ሁስቱ አሳቦችም፡-

1. «መናፍስት» (ኢዮብ 1:6፤ 2:1 እና ዘፍጥረት 6:2) እና

2. «የእግዚአብሔር ልጆች» እነዚህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታውን ስጦታ የተቀበሉ ናቸው (ዮሐንስ 1:12፤ 3:8፤ ኤፌሶን 1:5፤ ሮሜ 8:14፤ ወዘተ.)።

የክርስቶስ አምላክነት በሁለቱም ኪዳኖች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እንደ ተቀመጠ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ሥላሴን በተመለከተ የብሉይ ኪዳንን መረጃ በሚከተለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን። አሁን ግን ወደ አዲስ ኪዳን መረጃ መመልከት አለብን:-

> «በመጀመሪያው ቃል (ሎጎስ) ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም ... ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐንስ 1:1-5 እና 14)።
>
> «በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐንስ 1:10-12)።
>
> «እርስዋንም:- ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል አላት። ከእርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው:- ኃጢአትን እንኳ የሚያስተሰርይ ይህ ማን ነው? ይሉ ጀመር» (ሉቃስ 7:48-49)።
>
> «እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር ... ፈቅዶአልና። በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል» (ቈላስይስ 1:19 እና 16-17)።



> «ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ...» (ዕብራውያን 1:2-3)።
>
> «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» (ፊልጵስዩስ 2:6-7)።
>
> «እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ (መሢሕ) በሥጋ መጣ። እርሱም [ክርስቶስ] ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን» (ሮሜ 9:4-5)። (እዚህ ላይ ትርጉሙ የሚወሰነው በምንጠቀመው ሥርዓተ-ነጥብ ሲሆን፥ ይህም በመጀመሪያዎቹ መዛግብት ላይ አልነበረም።)
>
> «ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው» (2ኛ ቆሮንቶስ 4:4)።
>
> «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (የሐዋርያት ሥራ 20:28)።
>
> «የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» (1ኛ ዮሐንስ 5:20)።
>
> «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥

መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል» (ቲቶ 2፡11-14)።

ምናልባት እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የራሱ የክርስቶስ ቀጥተኛ ቃላት አይደሉም የሚል ተቃውሞ ይነሣ ይሆናል። ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና ይህን ለማጠናከር የክርስቶስን ቃላት ቀጥለን እንጠቅሳለን፡-

«አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላከም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል» (ራእይ 21፡6-7)።

«ከዚያም በኋላ ቶማስን (ከትንሣኤ በኋላ)፡- ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፡- ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፡- ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው» (ዮሐንስ 20፡27-29)።

ቶማስ ያመነው ምን ነበር? ጌታው ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ አምኗል። ክርስቶስም እንዲያምን አበረታታው እንጂ፥ ይህን እውነት አልካደም። ቶማስን ወይም ደግሞ ዛሬ እኛን ለማታለል አልፈለገም።

«እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። ኢየሱስ፡- ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም፡- ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም ስለ ስድብ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት» (ዮሐንስ 10፡30-33)።

ኢየሱስ ሰው ብቻ መሆኑን በመግለጽ ከድንጋይ መወገር ለማምለጥ አልሞከረም። ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ በእርግጥ ይህን ያደርግ ነበር። ይልቁንም የዚህን ተገላቢጦሽ ተናግሯል፡-

«እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር።



ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው። ፊልጶስ፡- ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም አለው፡- አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ፡- አብን አሳየን ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» (ዮሐንስ 14፡6-10)።

ነቢያት ሁሉ እንደ ተራ ሰዎችና ኃጢአተኞች ሲታዩ፥ ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ማስቀመጡ ትልቅ ነገር ነው፡-

ኢየሱስ «ኃጢአት ያላወቀው» ነበር (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

ኢየሱስ «ኃጢአት አላደረገም» (1ኛ ጴጥሮስ 2፡22)።

ኢየሱስ «ከኃጢአት በቀር... እንደ እኛ...ነው» (ዕብራውያን 4፡15)።

በኢየሱስ «ኃጢአት የለም» (1ኛ ዮሐንስ 3፡5)።

ይህም «ንጹሕ» የማርያም ልጅ በሚናገረው የቁርዓን ክፍል ተጠናክሯል (ሱረቱ 19፡19)።

የእነዚህን ሁሉ ዐረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚያዛባ «ማብራሪያ» የለም። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? የሚከተለው ምዕራፍ መልሱን ይሰጣል።

## በሥላሴ ትምህርት ላይ የእስልምና ተቃውሞ

ከዚህ ምስጢር በላይ በተሳሳተ መልኩ ከግንዛቤ ላይ የዋለ ነገር የለም። ገና ከጅምሩ ሥላሴ የሚለው ቃል የሥነ-መለኮት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዳልሆነ ለመግለጽ እንፈልጋለን። እንደ ሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት ከመደንገግ ይልቅ ተጠቁሞ የሚታለፍና ከሰብአዊ መረዳትም የላቀ ነገር ነው። በግልጽ መቀበል ያለብን ነገር ቢኖር፥ ሥላሴን ለመረዳት ሰው የሚያደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ፥ በማመሳሰል መንገድም እንኳ ቢሆን ከንቱ መሆናቸውን ነው። ለዚህም ቀላሉ ምክንያት የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመረዳት ስለማንችል ነው። ሰው ሊረዳው የሚችለውና ለደኅንነት

የሚያስፈልገው ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተቀምጧል። ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የምንችለው ሁሉ ተገልጿል። ነገር ግን በዚያ መገለጽ የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ገጽታ ለማወቅ እንችልም። ያ ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከአእምሮአችን ያነሰ ይሆን ነበር። በዚህም መሠረት በሙስሊም «ሊቃውንት» የሚቀርቡትን እንደሚከተለው ያሉ ደካማ ክርክሮችን አንቀበልም፦

«በሁሉም የስሌት ሕጎች ሦስት በአንድ ሲባዛ ሦስት ይሆናል። ነገር ግን በክርስትና ስሌት ሦስት በአንድ ሲባዛ አንድ ይሆናል ... እስተውሎታችንን እንዳንጠቀምና የቤተ ክርስቲያንን ጭፍን እምነት ለመረዳት እንዳንሞክር በካህናት ተነግሮናል። ስለዚህም ያ የክርክሩ ዐቢይ ነጥብ ነው። እንድናምን የተጠየቅነውን ነገር ለመረዳት ከአምላክ የተሰጠንን የእስተውሎት ኃይል እንድንጠቀም አልተፈቀደልንም። በእነዚህ ትምህርቶች ላይ ያለን እምነት ዕውር፥ የማይጠየቅ፥ ፍጹም መሆን አለበት! እነዚህን እምነቶች ለመረዳት ብሎ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው፥ በሙሉ ቅንነት ቢሆንም እንኳን ወደ ዘላለም ጥፋት ወረደ ማለት ነው።»

የጥቅሱ የመጀመሪያው ክፍል ደካማ ከሆነ፥ ሁለተኛው ክፍል መርዘኛ ቅጥፈት ነው። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትንሽ እንኳ የሚያውቅ ሰው የትምህርቱ ሁሉ ዓላማ ማሳወቅ እንደሆነ አይስትም፦

> «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን ... ታውቁ ዘንድ ነው» (ኤፌሶን 1፡ 17 ና 18)።

> «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌሶን 3፡ 16-19)።



ተመሳሳይ መልእክት ያላቸው ሌሎች በርካታ ምንባቦች ሊጠቀሱ ይችላሉ። እስተውሎታችንን እንድንጠቀምበት ብንበረታታም ከግንዛቤአችን በላይ የሆኑ ነገሮች ደግሞ አሉ። ሃያስያኑ እንደ ዘላለማዊነት፥ መንግሥተ ሰማያት፥ እግዚአብሔር፥ ወዘተ... የሚሉትን ይቅርና እንደ የትየለሌ ያሉትን ጽንሰ አሳቦች እንኳን እሳማኝ በሆነ ሁኔታ ማብራራቱ እንቆቅልሽ ይሆንባቸው ይሆናል።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድቼ ነው ብሎ የሃይማኖት መጽሐፍ የሚጽፍ ከሆነ፥ አድማጮቹ ወይም አንባቢዎቹ ለመረዳት የማይችሉትን ነገር ከመጻፍ እንደሚቆጠብ ጥርጥር የለውም። ይህንንም የሚያደርገው በመጀመሪያ ደረጃ መልእክቱ ለመረዳት የማያዳግት እንዲሆን ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ግን ደራሲው ራሱ ለመረዳት የማይቻለውን ነገር ሊያስተውል ስለማይችል ነው! ሥላሴን ለመረዳት ያለመቻሉ ዋናው ምክንያት «ዝም ብሎ ሰው-ሠራሽ ንድፈ-አሳብ» በመሆኑ ነው የሚለው ወቀሳ ራሱ አሉባልታ ነው።

ብዙ ጊዜ «ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሆነ፥ በማርያም ማኅፀን በነበረ ጊዜ፥ በእራስነቱ ወይም በመቃብር ውስጥ በሆነ ጊዜ ዓለምን የሚያስተዳድረው ማን ነበር?» የሚል ጥያቄ እንሰማለን። እስኪ የሚከተለው ምሳሌ መልሱን ይስጠን፦ የውኃ መቅጃ ባልዲ ተሸክሜ ወደ ውቅያኖስ ወረድሁና ጨዋማውን ውኃ ሞላሁት። በውቂያኖሱ ውስጥ ያሉት ዓሦች ሁሉ ምን ይገጥማቸዋል? ምናልባት በትክክል፦ «ለምን? ይህ ከዓሣው ጋር ምን ግንኙነት አለው?» ትሉ ይሆናል። እኔም፦ «ዓሣ ካለ ውኃ ሊኖር አይችልም - ውኃውም አሁን በባልዲ ውስጥ ነው» ብዬ እመልሳለሁ።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ በነበረ ጊዜ፥ በሁሉም ስፍራ በመገኘት ችሎታው፥ በሌሎችም ስፍራዎች ሁሉ ነበረ።

አንድ ነገር ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እግዚአብሔርን የሆነው ክርስቶስ አልነበረም። ይልቁንም እግዚአብሔር ክርስቶስን ሆነ። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በሌላ በየትኛውም ስፍራ እስከማይሆን ድረስ ነበር ማለት አይደለም። ያማ እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ውስን ማድረግ ነው። «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡ 19)።

ብዙ ጊዜ ግዴለሽነት የሚታይባቸው ዐረፍተ ነገሮች ተሠርተዋል፡-

> «ስለ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቸኛው ጥቅስ የሚገኘው በ 1ኛ ዮሐንስ 5፡7 ሲሆን፡- <የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው፥ ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ > ይላል።»

ሃያሰያን እንደሚናገሩት ይህ በጣም ዘመናዊ በሆኑ ቅጂዎች ውስጥ በኢታሊክስ የጽሑፍ አጻጻል ስልት የተጻፈው ጥቅስ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባኤ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገባ እስከ ተደረገበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ለማስተማር ከምትጠቀምባቸው መካከል አልነበረም። ይህ የሚያመለክተው ክርስቲያኖች በራሳቸው ፈቃድ ጣልቃ እንዳስገቡት ነው። በቀጥተኛ አነጋገር የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ «የክርስትናው አካል የተደረጉት በኒቅያው ጉባኤ» ላይ ነበር። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የትኞቹ መጻሕፍት በሐዋርያት የተጻፉና የትኞቹ ደግሞ ምናብ ወለድና አፈ-ታሪክ ሆነው የተጨመሩ እንደ ሆኑ በከፊል የመረመሩት በዚህ ጉባኤ ላይ ነበር። ይሁንና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ከሞላ ጎደል ጠቅላላዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በየትም ሰፍራ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደ ነበሩ መታወቅ አለበት።

ይህ በእስያ፥ በአፍሪካና በአውሮፓ በመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በርካታ ጽሑፎች መረጃ ተደግፎአል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሥላሴ የሚናገረው አንድ ጥቅስ ብቻ እንደ ሆነ የሚናገረው ሂስ ትክክል ነው ወይስ አይደለም?

የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ገጽ በመግለጥ የሚከተለውን እነባለሁ፡-

> «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።»

«እግዚአብሔር» የሚለው ቃልና ጠቅላላው ምንባብ በዕብራይስጥ ስለ ተጻፈና «እግዚአብሔር» የሚለውም የአማርኛ ቃል ስለ ሆነ፥ በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምናገኘው «ኤሎሂም» የሚለውን ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ማለት ኤል ወይም ኤላህ መሆኑ ነው። «ኤሎሂም» ማለት እንግዲህ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት



«እግዚአብሔሮች» ማለት ነው። ትንሽ ፈቀቅ ብለን በቁጥር 26፡- «ኤሎሂም አለ፡- ሰውን . . . እንፍጠር»

> የሚል እናነባለን። እንደገናም በምዕራፍ 11፡7 የሚከተለውን እናገኛለን፡- «ኑ፥ እንውረድ . . . ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው»።

«እኛ» የሚለው ማንን የሚወክል ነው?

መልስ፡- «ኤሎሂም።» ይህን እንዴት እንረዳለን? ይህ የነገሥታቱ ዓይነት የብዙ ቁጥር አጠቃቀም ስልት ነውን? አይደለም፤ እንዲህ ያለ አጠቃቀም በዕብራይስጥ አይታወቅም ነበርና። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ደረጃ በደረጃ ስለሚገልጽ፥ በትምህርቱ ላይ የበለጠ ብርሃን ያረፈው በኋላ ነው። ከዘዳግም 6፡4 ጀምሮ የሚከተለውን እናገኛለን፡-

> «እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።»

ወይም፡-

> «አንተም ያህዌን የአንተን ኤሎሂምን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።»

ይሁንና የሚበልጠውን ብርሃን የሚፈነጥቀው የሚከተለው አጭር ዐረፍተ ነገር ነው፡-

> «አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።»

በዕብራይስጥ እንደሚከተለው ሊነበብ ይችላል፡-

> «ያህዌ ኤሉሄኑ ያህዌ ኢቻድ።»

ቃል በቃል ቢተረጎም ይህን ትርጉም ይሰጣል፡- «ጌታ እግዚአብሔሮቻችን፥ ጌታ አንድ ነው።»

> «ኢቻድ» የሚለው ይኸው ቃል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው በኋላ ስለ አዳምና ሔዋን በሚናገርበት ክፍልም ውስጥ አገልግሏል፡-

«ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ (ኢቻድ) ሥጋ ይሆናሉ» (ዘፍጥረት 2፡24)።

ያገቡ ሰዎች አንድ ግለሰብ ሳይሆኑ፥ ሁለቱ በአንድነት የተጣመሩ እንደ ሆነ መቼም እንረዳለን። እንደገና በኢሳይያስም በዚህ ትምህርት ላይ የበለጠ ብርሃን ተንጸባርቆበታል። የዚህ ምሥጢር ሙሉ መረዳት ለሰው ሊገባ በሚችል መልኩ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

«የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዥም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም» (ኢሳይያስ 44፡6)።

በተጨማሪም ይህን እናነባለን፡-

«የያህዌን ... ትልቅ በጎነት አሳስባለሁ። እርሱም (ለእስራኤል)፡- በእውነት ሕዝቤ፥ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው አለ ጃሹዋም (ኢየሱስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ዘመን የነበረው ስም ሲሆን፥ ወደ ቋንቋችንም ኢየሱስ በመባል ተተርጉሞአል) ሆነላቸው። በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው... እነርሱ ግን ዓመፁ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ ስለዚህ ተመልሶ ጠላት ሆናቸው» (ኢሳይያስ 63፡7-10)።

ለጊዜያዊ ጥቅሙ በማሰብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት መጠየቅን እምቢ ላለው ለንጉሥ አካዝ ነቢዩ እንዲህ በማለት ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል፡-

«ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳይያስ 7፡14)።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳይያስ 9፡6)።



አንዳንድ ጊዜ «የኃያሉ አምላክ ድንቅ መካር» ተብሎ መነበብ እንዳለበት ይነገረናል። ይህ እውነት አይደለም! በመጀመሪያው የዕብራይስጥ መዛግብት ውስጥ «ሼል» ወይ «የ» የሚል ነገር የለም።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 8፡58 መሠረት የሚከተለውን እንግዳ ዐረፍተ ነገር በግልጽ ተናግሯል፡-

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ (ነኝ) አላቸው።» ከዚያም አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ።

ለምን? ምክንያቱም «እኔ ነኝ» የሚለው «ያህዌ» ማለት ስለ ሆነ፥ ከአብርሃም በፊት እኔ ነኝ የሚለው ሰዋሰው የክርስቶስን ዘላለማዊ ሕልውና ያመለክታልና ነው።

ይህ ከብሉይ ኪዳን ጋር ፍጹም የሆነ ኅብረት ስላለው፥ እኛም እንደዚሁ እንቀበለዋለን። በዚህም ሆነ በሌሎች ለፍራዎች በኢየሱስና ስለ ኢየሱስ የሚናገሩትን ዐረፍተ ነገሮች ለመረዳትና በትክክልም ለመገምገም የምንችለው በብሉይ ኪዳን የመገለጽ ብርሃን ብቻ ነው፡-

«እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐንስ 10፡30)።

«አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው» (ዮሐንስ 10፡33)።

«እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐንስ 14፡9)።

«ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ የእግዚአብሔር አካል እንደ ሆነ ለመናገር ምንም ሥልጣን የላትም» ይላሉ ሚስተር ጁማል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት መልስ ይሰጣል፡-

«አሕዛብ ለምን ያጕረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፡- ማሰርያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል። በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል። በዚያን ጊዜም በቍጣው ይናገራቸዋል፥በመዓቱም ያውካቸዋል። እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን

> ላይ። ትእዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ። በብረት ብትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ» (መዝሙር 2፡1-9)።

ምንም እንኳ የትኛውም ዓይነት ማመሳሰያ ብቃት የሌለው ምስል ብቻ ቢሆንም፥ የሚከተለው ቀላል ገለጻ ሥላሴን ከአንድ አንጻር ብቻ እንድንመለከተው ያደርገናል፡-

አንድ ጠብታ ውኃ ወደ አንድ ኬሚስት (ተማራማሪ) ውሰድና የግምገማ ውጤቱን እንዲያሳውቅህ ጠይቀው። የሁለት እጅ ሃይድሮጂንና የአንድ እጅ ኦክስጂን ውህድ መሆኑን ይነግርሃል። ይህንኑ የውኃ ጠብታ ለፊዚክስ አዋቂ ብትወስድለት፥ ፈሳሽ ነገር እንደ ሆነ ይነግርሃል። አሁንም ጥቂት በረዶ ውሰድና እንዲሁ ጠይቅ። ኬሚስቱ እንደ መጀመሪያው ሲመልስ፥ ፊዚስቱ ጠጣር ነገር ነው ይልሃል። አሊያም የሙከራ ቱቦ ውስጥ የምላ እንፋሎት በመውሰድ ከኬሚስቱ ተመሳሳይ ውጤት፥ ከፊዚስቱ ግን የተለየ ውጤት እናገኛለን። ፊዚስቱ ጋስ ነው ይላል።

እጅግ አከብሮት በተሞላ መንገድ በዚህና በሥላሴ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለመጠቆም እፈልጋለሁ። ውኃ፥ በረዶ፥ ወይም ትነት የቅርጽ ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ፥ የሁለት እጅ ሃይድሮጂንና የአንድ እጅ ኦክስጂን ውህድ እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ እግዚአብሔርም በተለያዩ «መገለጫዎቹ» ሁሉ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ነው። ምናልባት የሕይወት ጀማሪና አቆዩ የሆነውን ውኃ በፈጣሪ አባት፥ ሊጨበጥ የሚችለውን በረዶ አዳኝ በሆነው በልጁ፥ እና ባመዛኙ የማይታየውንና ለመቆጣጠርም የሚያዳግተውን ዳሩ ግን ኃይልን የሚወክለውን ትነት፥ ለሚፈልጉት ሁሉ እግዚአብሔርን በሚገልጸውና ለአማኙም በጽድቅ እንዲኖር ኃይል በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ልንመስል እንችላለን። ይሁንና ሦስቱም የእግዚአብሔር ገጽታዎች እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።

ሌሎችም ማመሳሰያዎች አሉ። ሰው ሥጋ፥ ነፍስና መንፈስ አለው። የፀሐይ ጨረርም ብርሃን፥ ሙቀትና የኬሚካል ኃይል አለው። እሳት፥ ብርሃንና ሙቀት ሦስት ቢሆኑም፥ በሌላ በኩል ስንመለከት ግን አንድ ናቸው። እንደዚሁም አእምሮ፥ አሳብና ንግግር አንድ ዓይነት ሲሆኑ፥ እርስ በርሳቸው የሚለያዩባቸው ሁኔታዎችም አሏቸው።



## ስቅለትን በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

በክርስቲያን-ሙስሊም ውዝግብ ውስጥ ሌላው ከፍተኛ ጉዳይ ስቅለት ነው። ይህም ብዙውን ጊዜ ሞቅ ያለ ክርክር ያስነሣ ነጥብ ነው። ለክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ድርድር የማይሆን ነገር ነው። ለሙስሊሙም ቢሆን ድርድሩ ቦታ የለውም። ከቁርዓን መሠረታዊ ዐረፍተ ነገሮች አንዱ እንዲህ ይላልና፡-

> «አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ፥ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው» (ሱረቱ 4፡157-158)።

ዐረፍተ ነገሩ እንደዚህ ከወንጌሉ ሙሉ ለሙሉ በተቃረነ መንገድና በፍጹም «ድጋፍ» ሳይሰጠው እንዲጻፍ ያደረገው ምንድነው? (ገጽ5-7 ተመልከት)። የወቅቱን ሁኔታ መልሶ ማስቀመጡ ቀላል አይደለም። ነገር ግን በመሐመድና በጊዜው በመዲና በነበሩ አይሁዶች መካከል የነበሩ ግንኙነቶች እየሻከሩ መጡ። ከዚህም የተነሣ በሁለቱም ወገኖች መካከል የነበረው አመለካከት የበለጠ ጠላትነትን እያሳደገ መጣ። ከነቢያት ሁሉ በላይ ስላስቀመጠው፥ ስለ ኢየሱስ በጣም ከፍተኛ አሳብ እንደ ነበረው አያጠራጥርም።

መሐመድ የሚከተለውን እንደተናገረ ተዘግቧል፡-

> «እኔ ከሰዎች ሁሉ በላይ የማርያምን ልጅ እቀርበዋለሁ» «በዚህ ምድራዊ ሕይወትም ሆነ በሚመጣው ሕይወት ከሰዎች ሁሉ በላይ ወደ ኢየሱስ እጠጋለሁ» (ሳሂህ ሙስሊም፥ ቅጽ 4፥ ገጽ 1260-1261)። እንዲህ ያለ ዐረፍተ ነገር እንዲጻፍ የገፋፋው ምንድነው?

ይህ አመለካከቱ ግን ጠላቶቹ አይሁዶች በዚህ ዓይነቱ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ላይ በቂ ኃይል ኖሯቸው ያጠፉታል ብሎ እንዲያስብ አይፈቅድም ነበር።

የከስተቶችን ቅደም-ተከተል ባስያዙት ሰዎች ዘገባ መሠረት፥ ሱረቱ 4 የተጻፈው በመሐመድ የመዲና ኑሮ አጋማሽ ላይ ነው። ይህም በግምት 5 ኤ. ኤች. ይሆናል። በሃዲስ ውስጥ ከተመዘገቡት ከበርካታ ክስተቶችና ማስታወሻዎች አንጻር፥ ይህ ክፍለ-ጊዜ በአይሁዶችና በሙስሊሞች መካከል ጫን ያለ ተቃርኖ የተስተዋለበት ነው።

አንድ ነቢይ ከተራው ሰው ከፍተኛ የበላይነት ስላለው፥ መከራ መቀበል ወይም መሸነፍ (መስቀሉ ማለት ለመሐመድ ይህን የመሰለ ነበር) የማይቻል ነገር ነው። ኢየሱስ ለመሐመድ በጣም ትልቅ ሰው ነበር። ይህም ከነቢያት ሁሉ በተለየ መልክ በመሐመድ ትምህርት መሠረት ኢየሱስ ከድንግል የተወለደ ብቸኛው ሰው በመሆኑ፥ ሕያው ሆኖ ወደ ሰማይ በማረጉ፥ ተመልሶ የሚመጣ በመሆኑ፥ ኃጢአት የሌለበት በመሆኑ፥ «የእግዚአብሔር ቃል» እና «ከእግዚአብሔር የመጣ መንፈስ» ተብሎ በመጠራቱና «በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው የተከበረ» በመሆኑ ነው (ገጽ 127-128 ተመልከት)። መሐመድ ክርስቶስ ሊፈጽመው ስለ መጣው የስርየት ሥራ አልተረዳም ነበር። ያለዚህም የስርየት ሥራ የመስቀል ላይ ሞቱ ትርጉም ሊሰጥ አይችልም።

ቀጥለን እንደምንመለከተው፥ መሐመድ ከወንጌል ጋር በመጀመሪያ ይዘቱ በፍጹም አልተዋወቀም ነበር። በቁርዓን ውስጥ የምናገኘውና ስለ ኢየሱስ የተገለጸው እውቀት የተገለበጠው ከአዋልድ መጻሕፍት ወይም በጊዜው በዐረቢያ ከነበሩት ኮፕቲክ ክርስቲያኖች (የኢየሱስ ባሕርይ መለኮታዊ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ) በአፈ-ታሪክ መልክ የቀረበና እውነትነቱ ያልተረጋገጠ ነው።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፥ አሁንም በሱረቱ 3፡55 እና 19፡33 ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን አሳማኝና ጥንቃቄ የተሞላበት ትርጉም ለመመልከት እንፈልጋለን፡- «ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ፥ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ» (እንድትሞት አደርጋለሁ)። ይህም እንደ አሊ እብን አባስ፥ አቡዱላህ እብን ሳሊህ፥ ሙአዌሄህ፥ አብን ዒሳቅ፥ ሳልማ እና ዋሃብ እብን ሙናቢህ የመሳሰሉ በርካታ የጥንታዊ መዛግብት ዘጋቢዎች እንደሚረዱት ነው። እንዲሁም «ሰላምም በኔ ላይ ነው፥ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን፥ (እንደገና) ሕያው ኾኘ በምቀሰቀስበትም ቀን» ሲል የተቀመጠበትን ቅደም ተከተል ቸል ልንል አንችልም፡- መወለድ - መሞት - መነሣት።



መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው ኢየሱስ የመስቀል ሞት ካልሞተ፥ እንግዲህ መቼ ሞተ? በቁርዓን በተገለጸው መሠረት መሞት ነበረበት (ሱረቱ 4፡159፤ 19፡ 33፤ 3፡55) (ዶክተር ኤ. ሃቅ)።

ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ (በሌላም ስፍራ) ስለ ስቅለት ህልቆ-መሳፍርት የሌላቸው ማጠናከሪያዎች አሉአቸው። ከወንጌላት ውስጥ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው ታሪክ የሚያተኩረው በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ በመጨረሻው ሳምንት ስለ ሆነውና ስለ ሞቱ ነው። ይህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የምናገኘው ከስርየት ትምህርትና ከመሥዋዕት አቀራረብ ጋር ሙሉ ለሙሉ የተስማማ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ፥ የመሢሑ የመሥዋዕትነት ሞት በብሉይ ኪዳን ስለ ተተነበየ፥ «ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን»፡-

> «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ እዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ... ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ... እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ» (ኢሳይያስ 53፡4-12)።

> «ወደ ሞትም አፈር አወረድኸኝ ... እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ ... እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» [መዝሙር (22)፡15-18]።

ዓለማዊ ታሪክ ስቅለቱን ያጠናክረዋል።

የአዲስ ኪዳን መዛግብት በታሪክ ሰዎች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝተዋል። ከ5000 በላይ የሚሆኑና ከእጃችን የሚገኙ መዛግብት እንዲህ ያለ ከፍተኛ ተአማኒነት ስላላቸው፥ የስቅለቱ እውነታ ሊካድ

አይችልም። ምንም እንኳ ከጥቂቶቹ በስተቀር፥ መዛግብቶቹ የመጀመሪያዎቹ መዛግብት ከተጻፉበት በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ባይጻፉም፥ ምስክርነታቸው እውን ነው።

ይሁንና የጊዜው ርቀት ሲታይ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደ ተገለጹት በሚገባ ተመዝግበው ለትውልድ የተላለፉ የዚያን ዘመን ታሪካዊ ክስተቶች የሉም።

ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተቶችን በተመለከተ መረጃዎችን እንደማይሰጥ ብዙ ጊዜ ተነግሯል። «የመነቃቃት ዘመን» በተባለው የፍልስፍና ጊዜ የክርስትና እምነት ከኋላ ቀር ሽቀጥ በመቆጠሩ፥ የሂሱን አግባብነት ለማረጋገጥ የተወሰደ ጊዜ አልነበረም። ከዚያም በኋላ፥ ነገሮችን እንደገና በትክክለኛ ስፍራቸው ለማስቀመጥ ከጥቂቶቹ በስተቀር የሞከረ ሰው የለም። (ዘመናዊ) የሥነ-መለኮት አዋቂዎች ተብዬዎቹም ከ«መነቃቃቱ ዘመን» የበቀለውን ይህን እኩይ ጽንሰ-አሳብ በሚገባ ተቀብለው ማስተማራቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ዳሩ ግን በበርካታ መስኮች የሳይንስ ዕድገት በመፋጠኑ፥ ክርስቲያኖች ከማንም በላይ ለእምነታቸው ድጋፍ አግኝተዋል!

> «እንደ ደብልዩ ኤም ራምሰይ፥ ኤድ. ሜየር እና ኤ.ቲ. ኦልምስቴድ የመሳሰሉት ታሪክ ጸሐፊዎች የአዲስ ኪዳን ታሪካዊ ጽሑፎችን በተመለከተ የአንዳንድ የሥነ-መለኮት ሰዎችን ከፍተኛ ጥርጣሬ በሚገባ ተቃውመዋል» («የአዲስ ኪዳን መዛግብት» በኤፍ. ኤፍ. ብሩስ)።

በአንዳንድ ሐቆች ላይ እናተኩራለን።

«5000 የሚሆኑ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ የአዲስ ኪዳን መዛግብት በሙሉ ወይም በከፊል አሉ። ከእነዚህ መዛግብት መካከል ይበልጥ የሚሻሉትና ጠቃሚ የሆኑት ወደ 350 ዓ.ም. አካባቢ የተጻፉት ናቸው።»

«የጽሑፍ መገኛዎቹን ከሌሎች ጥንታዊ የታሪክ ሥራዎች ጋር ብናወዳድረው፥ ምናልባት አዲስ ኪዳን በመዛግብቱ እውነተኛነት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ልናደንቅ እንችላለን። ለቄሣሩ ‹ጋሊክ ጦርነት› (በ58 እና 50 ዓ.ዓ. መካከል የተዘጋጀ) ከነበሩት በርካታ መዛግብት



ውስጥ፥ ዘጠኝ ወይም አሥሩ ብቻ ጥሩዎች ናቸው። ከእነዚህ መዛግብት ውስጥ እጅግ ጥንታዊው ከቄሣር በኋላ 900 ዓመታት ያህል ቆይቷል። ከሊቪ (ከ59 ዓ.ዓ. - 17 ዓ.ዓ.) 142 የሮም ታሪክ መጻሕፍት መካከል ሠላሳ አምስቱ ብቻ ይገኛሉ። ሚዛን ከሚደፉት ሃያ ከሚሆኑት መዛግብት ማከከል የመጻሕፍት ቁርጥራጮችን የሚያካትተውና ከመጽሐፍ ሦስት እስከ ስድስት ያለው አንዱ ብቻ የአራተኛው ምእተ-ዓመት ያህል ዕድሜ አለው። ‹ታሪኮቹ› ከተሰኘው የታኪተስ አሥራ አራት መጻሕፍት ውስጥ (100 ዓ.ም. አካባቢ) አራት ተኩሉ ብቻ ይገኛሉ። ከአሥራ ስድስት የ‹ዜና› መጻሕፍቱ ውስጥ አሥሩ ሙሉ ሆነው ሁለቱ ደግሞ በከፊል ይገኛሉ። የእነዚህ እሁን የሚገኙ ሁለት ታላላቅ ታሪካዊ ሥራዎቹ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ በሁለት መዛግብት ላይ ይደገፋሉ። አንደኛው የዘጠነኛው ምእተ-ዓመት ሲሆን፥ ሌላኛው የአሥራ አንደኛው ምእተ-ዓመት መዝገብ ነው። ከእናሳ ሥራዎቹ ውስጥ የሚገኘው መዛግብት ሁሉ (ዲያሎገስ ዲ ኦረቶሪቡስ፥ አግሪኮላ፥ ጀርማኒስ) ከአሥረኛው ምእተ-ዓመት ጥንታዊ ጽሑፍ የተገኙ ናቸው።»

«የቱሲዳይዴስ (460-400 ዓ.ዓ. አካባቢ) ታሪክ ከስምንት መዛግብት ውስጥ የምንረዳው ሲሆን ከሁሉም ጥንታዊው የ900 ዓ.ም. ዕድሜ አለው፤ ጥቂቶቹም የቁጠማ (የፓፒረስ) መጻሕፍት ቁርጥራጮች በክርስትና እምነት መጀመሪያ አካባቢ የተጻፉ ናቸው። የሄሮዶቱስንም ታሪክ (488-428 ዓ.ዓ. አካባቢ) በተመለከተ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንመለከታለን። ይሁን እንጂ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት የሥራዎቻቸው ጥንታዊ መዛግብት ከ1300 ዓመታት በኋላ ቢዘጋጁም እንኳ የሄሮዶቱስና የቱሲዳይዴስ ተአማኒነት አጠራጣሪ ነው የሚል የመከራከሪያ አሳብ፥ ማንም የጥንታዊ ዘመን ሊቅ አይቀበለውም።»

«ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ሁኔታ በዚህ ረገድ እንዴት የተለየ ነው! በሺህ ከሚቆጠሩት ከሌሎቹ ይበልጥ ጥንታዊ በመሆናቸው ከታወቁት ከአራተኛው ምእተ-ዓመት ሁለት ምርጥ መዛግብት (ኮዴክስ ቫቲካኑስ እና ኮዴክስ ሲናቲኩስ) በተጨማሪ፥ ከ100 እስከ 200 ዓመታት አስቀድመው የተዘጋጁ ብዙ የብራና ቅጂ የሆኑ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። መኖሩ በ1931 ይፋ የወጣው የቸስተር ቢቲ የመጽሐፍ ቅዱስ ብራና አሥራ አንድ የብራና ጽሑፎችን ክፍሎች ይይዛል። ከእነዚህም

ውስጥ ሦስቱ አብዛኛውን የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ይዟል። ከእነዚህም አንዱ የሐዋርያት ሥራንና አራቱን ወንጌላት ይዞ ይገኛል። የተዘጋጀውም በሦስተኛው ምእተ-ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ነው። ሌላው ለአብያተ ክርስቲያናት የተጻፉትን የጳውሎስን ደብዳቤዎችንና የዕብራውያንን መልእክት የያዘ ሲሆን፥ የተገለበጠውም በሦስተኛው ምእተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ (ማለትም ልክ ከ200 ዓ.ም. በኋላ) ነው። ሦስተኛውና የዮሐንስ ራእይን የያዘው በዚያው ምዕተ-ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ የተዘጋጀ ነው» (ከላይ እንደተመለከተው)።

ጥንታዊ የታሪክ ዘገባዎች ከጦርነቶች፥ ከጀግኖች ታሪክና በጊዜው ከሚገኙ መሪዎች በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደማያተኩሩ ሁላችንም እናውቃለን። ከዚህም የተነሣ እንደ ገሊላና ይሁዳ ባሉ የራቁ ቦታዎች የተፈጸሙ ጉዳዮች የታሪክን ዕይታ ያገኛሉ ብሎ ለመጠበቅ አስቸጋሪ ነው። ቢደረግ እንኳ የጦርነትና የቤተ መንግሥት ጉዳዮች ዋና ገጽታዎች ሆነው መቅረብ ነበረባቸው። ይህም ሆኖ የመጽሐፍ ቅዱስን ዘገባ የሚደግፉ ማጣቀሻዎች አሉ።

የሮማው ታሪክ ጸሐፊ ፕሊኒ በንጉሡ ነገሥት ትረጀን የትንሹ እስያ ግዛት ወደ ነበረችው ቢታንያ አውራጃ እንደ አገረ ገዥ ሆኖ (የሐዋርያት ሥራ 16፡7) በ112 ዓ.ም. ተልኮ ነበር። እዚያም ሆኖ በርካታ ደብዳቤዎችን ለንጉሠ-ነገሥቱ ጽፎ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ክርስቲያኖችን ይመለከታል። በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ፥ በመንደሮችና በገጠር አካባቢዎችም ጭምር፥ ክርስቲያኖችን እንዳገኘ ተናግሯል። የእነርሱ በፍጥነት መስፋፋት ትልቅ የማኅበራዊ ችግር ሆኖ ነበር። የባዕድ ቤተ አምልኮቶች ኀብኚ በማጣታቸው ምክንያት መዘጋት ነበረባቸው። በዓላቶቻቸውም ካለመከበራቸው የተነሣ፥ ከዚያ በኋላ ለመሥዋዕት የሚሆኑት እንስሳት ተፈላጊነት ቀርቷል። በፍጥነት በመስፋፋት ላይ የሚገኘውን የክርስትና እምነት መቃወም፥ ወይም ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ማዕቀብ መጣሉ ሁኔታውን አልለወጠውም። ፕሊኒ ሲዘግብ አሁን በብቁ አስተዳደሩ ሁኔታው እንደሚለወጥ አስተላልፎ ነበር! በክርስትና እምነት የጸኑት መገደል ነበረባቸው። እነዚህ ሰዎች በግልጽ እንቢተኞች ስለ ሆኑ መገደል እንደሚገባቸው ተናገረ። ዳሩ ግን እነርሱ በፈጸሙአቸው ጥፋቶች ግራ እንደ ተጋባም አምኗል። ተገድደው



እምነታቸውን የተዉ ሰዎች፥ ክርስቲያኖች በስብሰባቸው ጭካኔ የተሞላባቸውን ተግባራት እንደማይፈጽሙ አሳውቀውታል። ብቸኛው ጥፋታቸው ለሹማምንቱና አማልክቱ ሐውልቶች አለመስገዳቸውና ዳሩ ግን በተወሰኑ ቀናት (እሑድ እሑድ) ከፀሐይ መውጫ በፊት ተሰብስበው ለአምላካቸው (ኳሲ ዴኦ) ለክርስቶስ መዘመራቸው ነበር። በጥምቀታቸውም ዕለት ማንኛውንም ዓይነት ጥፋት ላለመፈጸም መሐላ ያደርጉ ነበር። ሕይወታቸው ምሳሌያዊ ነበር። በመካከላቸው ማታለል፥ ዝሙት፥ ስርቆት፥ ወይም እምነትን ማጉደል አልነበረም።

በቅዱስ ቁርባናቸው ጊዜ የተለመደ ምግብ እንጂ እንደ ታማው የሕፃናት ሥጋ አልበሉም። (ክርስቲያኖች «የክርስቶስን ሥጋ በመቀበላቸው» ብዙውን ጊዜ የሰውን ሥጋ ይበላሉ ተብለው ታምተዋል)። (ከ«ኢስ ኮሜሚር ኬይነር ሚት ታትሳሽን» በሚካኤል ግሪን በቀጥታ የተተረጎመ። የእንግሊዝኛ ርዕሱ «ራን አወይ ዎርልድ» በአማርኛ «የኮበለለ ዓለም» የሚል ነው።)

በፕሊኒ ዘመን የነበረው ቆርኔሌዎስ ታክቱስ የሮም መንግሥት ታላቁ ታሪክ ፀሐፊ ነበር። እርሱም ሲተርክ (በወንድሞችና በእህቶች መካከል ላለው «ፍቅር» ትኩረት መስጠታቸው ክርስቲያኖችን በሕዝብ ዘንድ በሐሰት እንደ ጋጠወጦችና የሰው ሥጋ በላዎች አስቆጥሯቸው ነበር) ክርስቲያኖች በወንጀሎቻቸው ምክንያት በኅብረተሰቡ ዘንድ ምን ያህል እንደ ተጠሉና በ64 ዓ.ም. ኔሮ በሮም ለተቀሰቀሰው የሰደድ እሳት መንስኤዎች ናችሁ በመባል ጥፋቱ እንደ ተላከከባቸው ይናገራል።

በጽሑፉም፡- «ክርስቲያን የሚለው ስም የተወሰደው በአገረ ገዢው በጲላጦስ ዘመነ-መንግሥት ከተገደለው ከክርስቶስ ነው። ለጊዜው ጋብ ብሎ የነበረው አጉል እምነት፥ እንደገና በመቀጣጠል ይህ በሽታ በተጀመረበት በይሁዳ ብቻ ሳይሆን፥ ክፉው ነገር ሁሉ እየመጣ በሚከበርበት በሮምም ሳይቀር ተስፋፍቷል።»

ከመሳፍንት ወገን የነበረው ታሲቱስ፥ ባጠቃላይ በዝቅተኛው መደብ ላሉት ሰዎች በተለይም ምሥራቃውያን ላሉበት ክርስትና ግድ እንዳልነበረው ግልጽ ነው። ስለ ሆነም የእርሱ ታሪካዊ መረጃ ከሁሉም በላይ ተቀባይነት ያለው ነው (ከላይ እንደተመለከተው)።

ታሪክ ጸሐፊው ታሉስ በ52 ዓ.ም. አካባቢ በሮም ሆኖ ጽፎ ነበር። ሥራዎቹ ግን ቢጠፉም፥ ከዚያ ውስጥ የነበረው አንድ ቁራጭ መልእክት በሁለተኛው ምእተ-ዓመት ጁሊዩስ አፍሪካኑስ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። በስቅለት ጊዜ በምድር ላይ ስለ ወደቀው ጨለማ (ማርቆስ 15፡33) የሚናገረው ጁልየስ አፍሪካኑስ እንዲህ ይላል፡-

> «በቅጽ ሦስት የታሪክ ዘገባው ታሉስ ለእኔ እንደሚመስለኝ ጨለማው የፀሐይ ግርዶሽ ነው ማለቱ ትክክል አይደለም በማለት ያስታውቃል።»

በጁልዩስ አፍሪካኑስ የቀረበውን ተቃውሞ ማክበር አለብን። ምክንያቱም ክርስቶስ በሞተበት የፋሲካ ዕለት ሙሉ ጨረቃ ስለ ነበር፥ ሙሉ የፀሐይ ግርዶሽ ሊኖር አይችልም። ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የዘገባው ክፍል ግን በአንደኛው ምእተ-ዓመት አጋማሽ አካባቢ የክርስቶስ ሞትና የአሟሟቱም ሁኔታዎች በሮም እንኳ ሳይቀር መታወቃቸውን ማሳየቱ ነው። በደንብ ከመታወቁ የተነሣ፥ ይህ ክርስቲያን ያልሆነ የታሪክ ጸሐፊ ዋጋ እንዳለው አድርጎ በማሰብ አስተያየቱን ሰጥቷል።

የሮማ ባዕድ አምላኪዎች በሃምሳዎቹ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ያወቁት (20 ዓመታት ከስቅለት በኋላ) ስለ መስቀሉ ብቻ አልነበረም። ለሚከተለው መረጃ ትክክለኛ ትርጉም ከሰጠነው፥ ስለ ኢየሱስ ትንሣኤም ጭምር ያውቁ ነበር። በንጉሥ ቀላውዴዎስ ቄሣር (41-54 ዓ.ም.) ዘመነ መንግሥት የተዘጋጀ ከፍተኛ መታሰቢያነት ባለው የተቀረጸ ጽሑፍ ላይ ንጉሡ ሙታን ከመቃብር እንዲወጡ ስለ መደረጋቸው በቀረበለት ዘገባ መበሳጨቱን ገልጸ የዚህ ዓይነቱ ነገር ቢደገም የሞት ቅጣት እንደሚያስከትል ያስጠነቀቃል። ይህ የመታሰቢያ ጽሑፍ (ቅርጽ) የሚገኘው የት ነው? ካልጠፉ ስፍራ፥ በናዝሬት! (ከላይ እንደተመለከተው)።

ጆሲፈስ በሮም ላይ በተነሣው የዓመፅ ንቅናቄ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት የአይሁድ መሪዎች አንዱ ነበር። ከ70 ዓ.ም. በኋላ (ኢየሩሳሌም የወደቀችበትና የፈራረሰችበት ዓመት) በመላው የሮም ኅብረተሰብ ዘንድና በተለይም በቤተ መንግሥት አካባቢ ለይሁዲ ሃይማኖት (ጁዳይዝም) መልሶ ስፍራ ለማስገኘት ሞክሯል። ስለዚህም «አንቲኩቴትስ ዩዴይካ»



(93 ዓ.ም.) እና «ዲ ቤሎ ዩዴይካ» (75-79 ዓ.ም.) በተባሉት መጻሕፍት ውስጥ ስለ አባቶቹ ሃይማኖት በበለጠ ለሮም ሕዝብ ለማሳወቅ ጽፎአል ... በዚህ ውስጥ ከአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናውቃቸውን በርካታ ገጸ-ባሕርያት እናገኛለን፡- ጲላጦስ፥ ሐናንያ፥ ቀያፋ፥ ሄሮድስ፥ ቁሬኔዎስ፥ ፊልክስ፥ ፊስጦስና ሌሎችም። እንዲሁም ደግሞ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ስለ ስብከቱ፥ ስለ ጥምቀቱና ስለ ሞቱ ጽፎአል።

> «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ የሚባል ጠቢብ ሰው ነበር። እርሱም የድንቅ ሥራዎች አድራጊ፥ እውነትን በቅንነት የተቀበሉት ሰዎች መመህር በመሆኑ ሰው ነው ብሎ መጥራቱ አግባብነት ያለው አይመስልም። ወደ ራሱም በርካታ አይሁዶችንና አሕዛብን ሳበ። እርሱም ክርስቶስ (መሢሑ) ነበር። ጲላጦስ በመካከላችን ባሉት አለቆች አሳሳቢነት ለመስቀል ሞት አሳልፎ በሰጠው ጊዜ፥ በመጀመሪያ የወደዱት ሰዎች አልተለዩትም ነበር። ምክንያቱም በሦስተኛው ቀን ሕያው ሆኖ ተገልጾላቸዋልና። ይህም የሆነው ቅዱሳን ነቢያት እርሱን በተመለከተ ይህንና ሌሎች በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ አስደናቂ ነገሮች እንደ ትንበዩት ነው። እንዲሁም ከእርሱ የተሰየመው ነገድ-ክርስቲያን ዛሬም ከምድር ገጽ አልታጣም» («አንቲ ኩ ቴትስ ዩዴይካ» 18፥111፡3) (ከላይ እንደተመለከተው)

በገና አካባቢ የፕላኔቶችና የከዋክብትን እንቅስቃሴ ለማመልከት የተዘጋጀውን የሞዴል (ፕላኔተሪየም) ብንጎበኝ፥ ምናልባት በጣም የሚያስደስት ከስተት መመልከታችንን እንመሰክር ይሆናል። በእርግጥ ፕላኔተሪየም አንድ ሰው ከዋክብትን በቴሌስኮፕ (የሩቅን አቅርቦ በሚያሳይ መሳሪያ) ከሚመለከትበት ሁኔታ ጋር በማመሳሰል ግር መሰኘት አይገባም። ፕላኔተሪየም ትልቅና ጨለማ ክፍል ያስፈልገዋል። ከክፍሉ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ በጨለማው ጣሪያ ላይ ቀጫጭን ጠንካራ የብርሃን ጨረሮችን የሚረጭ በጣም የተወሳሰበ መሣሪያ ይቀመጣል። ትመልካች ወደ ላይ አንጋጦ በሚመለከትበት ሰዓት፥ ልክ ከምሽቱ ብሩህ ሰማይ ሥር ያለ ይመስለዋል። ከዋክብቱም በኮምፒውተር አማካኝነት ዘፈቀደአዊ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዋክብትን በሙሉ፥ ፕላኔቶችና በርቀት ያሉት ኔብሌዎች (በቡድን ሆነው እጅግ የተጠጋጉ ከዋክብት) ጭምር በተወሰነ ጊዜና ቦታ በተፈጥሮ ሰማይ ላይ እንዳሉ የከዋክብት ክምችቶች

ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። ስማዩ ሲለወጥ እንዲሁ ሰው ሠራሹ የፕላኔተሪየም «ስማይ»ም ሊለወጥ ይችላል። በገና በዓል ስሞን የቤተ ልሔም ከተማ የምሽት ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ጊዜ ምን ይመስል እንደ ነበር ሊታይ ይችላል። የከዋከብት መንገድ የማይዛነፍ ከመሆኑም የተነሣ አንድ ሰው በታሪክ ውስጥ ማንኛውንም የምሽት ስማይ መልሶ መሥራት ይችላል። ይህም ኮሞስ=ሥርዓት ነው።

ያልሠለጠነ ተመልካች በፕላኔተሪየም እና በማንኛውም ጥንታዊ የምሽት መካከል ምንም ልዩነት አያገኝም። የመሪነቱን ሥራ የሚያከናውነው የሥነ ከዋከብት አዋቂው (አስተሮኖመሩ) ነው፤ ደማቆች የሰማይ ብርሃናት ጁፒተርና ሳተርን የሚባሉት ፕላኔቶች እንደ ጉልህ ኮከብ እስኪመስሉ ድረስ ተቀራርበው በአንድ ላይ ተጣምረው ጉልህ ደማቅ ኮከብ እንደሚመስሉ የሚያመለክተው። ይህ መጣመር በ6 ዓ.ዓ. በአጭር ጊዜ ውስጥ ሦስት ጊዜ ተደጋግሟል። ይህ ቁም ነገር ይኖረው ይሆን? እስኪ እንየው:-

> «ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ . . .» (ማቴዎስ 2፡1)

ይህ ታሪክ በሚገባ የታወቀ ነው። ነገር ግን ሄሮድስ በ4 ዓ.ዓ. እንደ ሞተ የታወቀ አይደለም። ከሁለት ዓመታት በታች የሆኑ የቤተ ልሔም ሕፃናት እንዲሞቱ ለምን ፈለገ? አንድ ሰው ገና በተወለደ ጨቅላና መሔድ በጀመረ ሕፃን መካከል መለየት አይችልም ይሆን? ይችላል። የምሥራቅ አገር አዋቂዎች ከመጡ ጀምሮ ረዥም የጊዜ ገደብ መቆጠር አለበት። ለዚህም ነው እንግዲህ ማረጋገጫ የፈለገው። ስለዚህ እንደ ታሪክ ጸሐፊዎቹ፥ ክርስቶስ የተወለደው በዜሮ ዓመተ ምሕረት ወይም በዲሴምበር (በታኅሣሥ) ውስጥ እንዳልሆነ ለመቀበል እንችላለን።

ስለ ሆነም ከዚህ በላይ የተጠቀሰው በክርስቶስ መወለድ ጊዜ እንደ ተፈጸመ አድርገን እንደመድማለን። እጅግ ከታወቁት የመጀመሪያ የከዋከብት ተመራማሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ጆሐንስ ኬፕለር ይህን የከዋከብት ሁኔታ በ1604 በወረቀት ላይ በማስላት በ6 ዓ.ዓ. አረጋግጧል።



> «በ1925 ዓ.ም. የጀርመን ሊቅ የሆነው ፒ. እስከኔብል በጥንታዊው ዓለም ዝነኛ የሙያ ተቋም በሆነው በባቢሎን በሚገኘው በሲፓር የአስትሮሎጂ (የከዋከብት ጥናት) ትምህርት ቤት ውስጥ በኒዎ-ባቢሎናዊ ኪዩኒፎርም (የተለየ የጽሑፍ አጣጣል) የተጻፈ «ፒስከስ» በተሰኘው የከዋክብት ክምችቶች ውስጥ ስላለው የፕላኔቶች አቅጣጫ የሚያስታውቅ ማስታወሻ አግኝቷል። በዚህም ላይ ጁፒተርና ሳተርን በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ በጥንቃቄ ተመልክተዋል። በቀን መቁጠሪያችን ላይ ሲሰላ ዓመቱ 7ዓ.ዓ. ነበር።» «በአይሁድ ባህል መሠረት፥ ፒስክስ የእስራኤል ምልክት፥ የመሢሑ (የክርስቶስ) ምልክት ነበር ... ጁፒተር ሁልጊዜም በሁሉም ሕዝቦች ዕድለኛና ክብር ኮከብ ሆኖ ይታሰባል። በጥንታዊ የአይሁድ ባሕል መሥረት ሳተርን የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚጠብቅ ተገምቷል።» ታስቱስ ከአይሁድ አምላክ ጋር ያስተካከለዋል...።
>
> «ከናቡከደነፆር ዘመን ጀምሮ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች በባቢሎን ኖረዋል። ምናልባትም ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹ በሲፓር የአስትሮሎጂ ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረው ይሆናል። በመሢሁ ‹የምዕራብ አገር› የከዋከብት ክምችት ውስጥ ይህ አስደናቂ የጁፒተር ከእስራኤል ጠባቂው ከሳተርን ጋር መጣመር የአይሁድ የሥነ-ክዋከብት ሊቃውንትን ስሜት በጥልቀት ሳያንቀሳቅስ አልቀረም። ምክንያቱም ይህ በኮከብ ቆጣሪዎች አስተሳሰብ መሠረት ታላቅ ንጉሥ ከምዕራብ አገር (ከባቢሎን በስተ ምሥራቅ ከአባቶቻቸው ምድር እንደሚመጣ ተመልክቶ ነበር። ለዚህ ነበር ጠቢባኑ ከምሥራቅ ተነሥተው በዓይናቸው እርሱን ለማየት የተጓዙት» («መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ታሪክ» በደብልዩ ኬለር)

ኬፕለር አንኳ የጸሐፈውን የሬቢ (መምህር) አባርባነልን ማጣቀሻ ካነበበ በኋላ፥ የተባለውን የክዋከብት ክምችት ዝርዝር ነገር ገሃድ ለማውጣት ተንቀሳቅሶ ነበር። ማጣቀሻው የሚከተለው ነበር፡-

> «የአይሁድ የሥነ-ከዋከብት ሊቃውንት ይህን ያልተለመደ ተጽዕኖ በዚሁ የከዋከብት ክምችት ላይ እንዳመካኙ ይነገራል። መሢሑ

ጁፒተርና ሳተርን በ‹ፒስክስ› ከዋክብት ክምችት ውስጥ በሚጣጣሩበት ጊዜ ይመጣል» (ከላይ እንደተመለከተው)።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ (2፡ 1-12) የሚከተለውን እናነባለን፡-

«ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል፡- የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም (አዲስ የተወለደ ሕፃን ወደሚፈልጉበት ወደ ንግሡ ከተማ) መጡ። ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፥ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር፤ የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። እነርሱም፡-

አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና።

ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት።

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን (የትኞቹን የዕድሜ ክልሎች እንደሚገድል ለማወቅ?) ከእነርሱ በጥንቃቄ ተረድተው፥ ወደ ቤተ ልሔምም እነርሱን ሰዶ፡- ሂዱ፥ ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው። እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ እነሆም፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው። ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፥ ወድቀውም ሰገዱለት፥ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት። ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ።»

የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ በሲፓር ከነበሩት ተመራማሪዎች ጋር ግንኙነት እንዳለው ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹ ኮከብ ቆጣሪዎች ከዚህ የተጠቀሰውን የኮከብ ክምችት በማየት የአይሁድን የአተረጓጐም አሳብ እንደ ተረዱ አናውቅም። ዳሩ ግን በግኝቶቹ ውስጥ አስደናቂ የሆነ ቁም ነገር አለ።

ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት አደነቁ፡-

«ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?» (ማቴዎስ 8፡27)።

ይህ የሆነው በገሊላ ባሕር ላይ ማዕበሉን ፀጥ ባሰኘ ጊዜ ነበር። እኛ ምናልባት እንዲህ ለማለት እንችል ይሆናል፡-

ከዋክብት እንኳ ዘገባ የሚያቀርቡለት ይህ ማን ነው?

ይህ በምንም ዓይነት ዘመናዊ የኮኮብ ቆጠራ ለማካሄድ ማበረታቻ አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ልምምድ ያወግዘዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ቸር ከመሆኑ የተነሣ እዚህ ላይ እንኳ የነገሥታትን ንጉሥ የፈለጉ ሰዎች እንዲያገኙት ፈቅዶላቸዋል።

እያንዳንዱ የወንጌል ታሪክ ጸሐፊ የስቅለቱን ሁኔታ በትልቅ ዝርዝር ጽፎታል።

የሙስሊሞች ክርክር ይህ ሁሉ ሊሆን ቢችልም (ሱረቱ 4፡15)፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ስለ ወሰደው፥ በመስቀል ላይ የተቸነከረው ሰው ኢየሱስ ይመስላል እንጂ እርሱ አይደለም ነው። ይህ ክርክር በሚከተሉት ነጥቦች ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም፡-

1. ከትንሣኤው በኋላ፥ ክርስቶስ ከ500 ለሚበዙ ክርስቲያኖች ተገልጾላቸዋል፤ እነርሱም እውነቱን የመሰከሩ ሲሆኑ፥ የምስማሩን ችንካርና በጦር የተወጋ ጎኑን አሳይቷቸዋል።
2. የሞተው የብሉይ ኪዳን «መጽሐፍ እንደሚል» ከብዙ ዘመን አስቀድሞ በትንቢት በተነገረለት መሠረት ነው።
3. ክርስቶስ ስለ ሞቱ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር።
4. የዓይን ምስክሮች (ሐዋርያት) መስክረውለታል።
5. የታሪክ ሰዎችም ዘግበውታል።

እንደ ሌሎች የእስልምና ጉዳዮች ሁሉ በዚህ ክስተት ላይ የሚሰነዘረው ክርክር በሙሉ የሚያርፈው በአንድ ሰው ምስክርነት ላይ ነው፤ ይህም ከሌላው መረጃ ሁሉ ጋር ተጻራሪ ነው። ብዙ ጊዜ የሚነሣው ሌላው ጥያቄ ማቴዎስ 12፡38-40ን ይመለከታል፡-

«በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና፡- መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።»

ሃያሲያን ሲጠይቁ፡- «ዮናስ በዓሣ አንባሪው ሆድ ውስጥ የቆየው እንዴት ነበር? ሞቶ ወይስ በሕይወት ነበር? ይላሉ። ማረጋገጫው «ዮናስ በዓሣ አንባሪው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበር ...» ስለሚል፥ ይህ በግልጽ ከዋናው ነጥብ ማፈንገጥ ነው። ምሳሌው ወይም መግለጫው ነጥቡን ለማብራራት እየሞከረ ነው። እዚህ ላይ የጊዜን ርዝማኔ ይመለከታል።

ክርስቶስ አስቀድሞ ብዙ ምልክቶችን እንደ ሰጠና ከዚህም ጥያቄ በኋላ ይህንኑ ምልክት መስጠት እንደ ቀጠለ እንመለከታለን። ምልክቱ ለማያምን ሰው በመጻሕፍት ዘገባ መሠረት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሆኖ ይታያል። እንግዲህ ሃያሲያኑ ሲናገሩ፥ ኢየሱስ ዓርብ ዕለት ጠዋት ተሰቀለ፤ ወደ 9 ሰዓት አካባቢ ሞተ፤ ከዚያም የበዓል ቀን ከመጀመሩ በፊት፥ ማለትም ከፀሐይ መጥለቅ ቀደም ብሎ ተቀበረ። ያም የዓርብንና የቅዳሜን ቀናት (2) ያካትታል። ምክንያቱም እሑድ ዕለት ከፀሐይ መውጣት አስቀድሞ ኢየሱስ ተነሥቷልና! በመቃብር ውስጥ የነበረው ከዓርብ ዕለት እስከ ቅዳሜና ከቅዳሜ ዕለት እስከ እሑድ ባሉት ሌሊቶች ነው። ስለዚህም የሦስት ቀናትን ቁጥር ለማግኘት አንችልም ይላሉ። ይህ የአንባቢውን የባሕል ግንዛቤ የሚጠይቅ በመሆኑ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው።

ከሁሉ አስቀድመን የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ፥ «ቀንና ሌሊት» የሚሉ ቃላት ሁልጊዜም ከተመሳሳይ ቁጥሮች ጋር እንደሚሰለፉ መረዳት አለብን («ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት» ወይም «አርባ ቀንና አርባ ሌሊት»



ወዘተ። እንጂ በፍጹም «ሦስት ሌሊትና ሁለት ቀን» ወይም «አምስት ቀንና አራት ሌሊት» አይሆንም።) በዚህም ዓይነት በዕብራይስጡ የቃላት አገባብ «ዩ-ለዬላ» ከእኛው የ«አንድ ቀን ማለትም 24 ሰዓታት ወይም በዚህ ክልል ውስጥ ከሚገኝ ክፍለ - ጊዜ ጋር ይዛመዳል። (1፡17፤ 1ኛ ሳሙኤል 3፡12፤ ኢዮብ 2፡13፤ ዘፍጥረት 7፡14፤ ዘጸአት 24፡18፤ 34፡28፤ ዘዳግም 9፡9-10፥ 18፥25፤ 10፡10፤ 28፡66፤ 1ኛ ነገሥት 19፡8 እና ማቴዎስ 4፡2 ተመልከት።)

ቀን በፀሐይ መጥለቅ ይጀምራል፤ ይህም 12 ሰዓት አካባቢ ማለት ነው። ኢየሱስ ዓርብ ዕለት በ9 ሰዓት ሞቷል። ይህ አንድ ቀን ተብሎ ተቆጥሯል። ቅዳሜውን ሙሉ ደግሞ ሞቶ «በምድር ልብ ውስጥ» ስለ ነበር ሁለተኛውን ቀን አስቆጠረ ማለት ነው። እንዲሁም ምናልባት በሦስተኛው ቀን አጋማሽ ላይ ማለትም እሑድ ዕለት በፀሐይ መውጫ ጊዜ ተነሥቷል። ይህም ሦስተኛውን ቀን ያሟላል። በሦስተኛው ቀን መነሣቱ በብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ተደግፋል (ሉቃስ 24፡21፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡4 ወዘተ)።

ለዚህ ዳጎስ ያለ ደጋፊ አሳብ ለማግኘት ከመጽሐፈ «አስቴር» ውስጥ አስቴር ለመርዶክዮስ ከምትናገርበት እናነባለን፡-

«... ለእኔም ጹሙ፤ ሦስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትበሉም፥ አትጠጡም፤ እኔና ደንገጥሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን በሦስተኛውም ቀን አስቴርም፡- ለንጉሡ መልካም ሆኖ ቢታይ ንጉሡ ወዳዘጋጀሁለት ግብዣ (እራት)... ዛሬ ይምጣ አለች» (አስቴር 4፡16-5፡5)። ለሦስት ቀናት ቢጾሙም፥ በሦስተኛው ቀን እራት በልተዋል። እንደዚሁም የጦቢያ መጽሐፍ 3፡12-13 ከብሉይ ኪዳን ዘመን በመተረክ (200 ዓ.ዓ.)፡- በእንደዚህ ዓይነት ቃላት ወደ ላይኛው ቤት ክፍል አመራች። ለሦስት ሌሊትና ቀን አልበላችም፤ አልጠጣችም። እግዚአብሔርም ከኀፍረት እንዲጠብቃት (በግድያ ወንጀል ስለ ተከሰሰች) እየጠየቀች መጸለይዋን አላቋረጠችም። ከዚያም በኋላ፥ በሦስተኛው ቀን ጸሎቷን በመፈጸም እግዚአብሔርን አመሰገነች» ይህ «ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ተነሣ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡4 ወዘተ) ከሚለው የአዲስ ኪዳን ዘገባ ጋር ይስማማል።

የኢየሱስን ዓለም- አቀፋዊነት በተመለከተ የእስልምና ተቃውሞ

ሙስሊሞች የኢየሱስን ዓለም-አቀፋዊ አባባል ለመቃወም የሚችሉትን ያህል ሙከራ አድርገዋል።

> «ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ» (ዮሐንስ 14፡6)።

ይህንንም ለመፈጸም ከሁሉ የተሻለው መንገድ እንደ ሕዝበ-እስራኤል ብሔራዊ ነቢይ በመቁጠር ዝቅ ማድረግ ሆኖ ቆይቷል። ስለ ሆነም መሐመድ እንደ ተላከላቸው ለሚነገረው ለአሕዛብ ኢየሱስ አስፈላጊነቱን ያጣል ማለት ነው።

እስልምና ኢየሱስ ክልላዊ ነቢይ መሆኑን ደጋግሞ ተናግሯል ብሎ ይከራከራል፡-

> «ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም» (ማቴዎስ 15፡24)።

> «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» (ማቴዎስ 1፡21) (ሕዝቡ የሚለው አይሁድን መሆኑ ነው።)

> አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ላካቸው፡- «በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ» (ማቴዎስ 10፡5-6)።

እዚህ ላይ የወንጌል ዓለም-አቀፋዊነት እጠያያቂ ተደርጓል። ለመሆኑ ይህ አባባል ትክክል ነውን? ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በአይሁዶች ብቻ ተወሰነ? የዚህ መልስ መሠረት የሚገኘው በዘፍጥረት 12፡3 ላይ ነው፡-

> «የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።»

የሚባረኩትም በአብርሃም፥ በትክክል ለማስቀመጥም በዘሩ ነው። ይህ በይስሐቅ የቃል ኪዳን መስመር ውስጥ ይገኛል፤ በመሆኑም ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ በውኃ ጉድጓድ ከሳምራዊቱ ሴት ጋር ሲወያዩ ሳለ (ዮሐንስ 4)፥ «መዳን ከአይሁድ» እንደ ሆነ ተናግሯል። «መዳን ለአይሁድ» እንዳላለ ልብ ማለት ያሻል።



አይሁዶች ብቻ የኢየሱስን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ። በእስራኤል ታሪክና በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር በተገኙ ጽሑፎች ብቻ ስለ ተያዘ፥ ማንም ሮማዊ፥ ሕንዳዊ፥ ወይም ጃፓናዊ ይህን ነገር ሊረዳው አይችልም ነበር። አይሁዶች ኢየሱስን እየጠበቁ ቆይተው ነበር። እርሱም አይሁዳዊ መሆን ነበረበት (ዘዳግም 18፡15)። እንዲያውም ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት ቤት መሆኑን ለማረጋገጥ የዘር ሐረጉም መገለጽ ነበረበት (ዘፍጥረት 49፡10፤ 2ኛ ሳሙኤል 17፡13)። በመሆኑም ምንም እንኳ በመጣላቸው ጊዜ ባያውቁትም፥ አይሁዶች ሁሉ መሢሕን በናፍቆት ሊጠባበቁ ኖረዋል።

አይሁዶች ብቻ ከተረዱትና ካወቁት በኋላ እርሱን በገሃድ ለማወጅ ይችሉ ነበር። ስለ ሆነም ሁሉም ሐዋርያትና ከሞላ ጐደል ሁሉም የመጀመሪያ ክርስቲያኖች አይሁዶች ነበሩ። እነርሱም ቢሆኑ በመጀመሪያ ይህን የመረዳት ትልቅ ችግር ነበረባቸው። እግዚአብሔር ለጴጥሮስ በኢዮጴ በቤቱ ሰገነት ላይ እስከ ተናገረበት ጊዜ ድረስ (የሐዋ:ያት ሥራ 10)፥ ወንጌሉን ለአይሁዶች ብቻ ይናገሩ ነበር። ለጴጥሮስ ብቻም ሳይሆን፥ ለሳውልም በደማስቆ መንገድ ላይ (የሐዋርያት ሥራ 9)፥ እና ለፊልጶስ ብቻውን ሳለ በጋዛ ስርጥ ባለው በረሃማ መንገድ ላይ (የሐዋርያት ሥራ 8) ተናግሯል። ለአሕዛብ ሁሉ የምሥራቹን ቃል ለማድረስ፥ ወደ ዓለም እንዲሄዱ ክርስቶስ ታላቁን ተልዕኮ ከሰጣቸው በኋላ እንኳ (ከማቴዎስ 28፡19-20)፥ ሐዋርያት ለአይሁዶች ብቻ ሰብከዋል። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ርቀው እንዲሄዱ መርቷቸዋል (የሐዋርያት 1፡8፤ ሉቃስ 24፡27 ተመልከት)።

ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፡-

> «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» (ዮሐንስ 16፡12-13) ብሏል።

ይህ ልምምድ በበዓለ ኀምሳ (ጰንጠ-ቆስጤ) ዕለት ተጀመረ።

በኢዮጴ እና በቆርኔሌዎስ ቤት ከተደረገው እንግዳ ልምምድ በኋላ ነበር ሐዋርያት ታላቁን ተልዕኮ በተለየ ብርሃን ማየት የጀመሩት። ይኸውም ብሔራዊ ሳይሆን ዓለም -አቀፋዊ ወንጌል እንደ ሆነ መገንዘባቸው ነበር።

«በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነው ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ። እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ የሚጸልይ ነበረ። ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል፡- ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ በግልጥ አየው። እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ፡- ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለው። መልአኩም አለው፡- ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ። እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል። የተናገረውም መልአክ በሄደ ጊዜ፥ ከሎሌዎቹ ሁለቱን፥ ከማይለዩትም ጭፍሮቹ እግዚአብሔርን የሚያመልክ አንዱን ወታደር ጠርቶ፥ ነገሩን ሁሉ ተረከላቸው ወደ ኢዮጴም ላካቸው።

«እነርሱም በነገው ሲሄዱ ወደ ከተማም ሲቀርቡ፥ ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ። ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም ተመስጦ መጣበት፤ ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ፤ በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት። ጴጥሮስ ሆይ፥ ተነሥተህ እርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ጴጥሮስ ግን፡- ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ አንዳች ርኵስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ። ደግሞም ሁለተኛ፡- እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፥ ወዲያውም ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ።

«ጴጥሮስም ስላየው ራእይ፥ ምን ይሆን? ብሎ በልቡ ሲያመነታ፥ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምዖን ቤት ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው፡- ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ እንግድነት ተቀምጦአልን? ብለው ይጠይቁ ነበር። ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ፡- እነሆ፥ ሦስት ሰዎች



ይፈልጉሃል፤ ተነሥተህ ውረድ፥ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው።»

ቆርኔሌዎስ የሆነውን ሁሉ ለጴጥሮስ ከገለጸለት በኋላ፥ ጴጥሮስ መልሶ እንዲህ አለ፡-

«እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ። የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህን ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ። ዮሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ ከገሊላ ጀምሮ በይሁዳ ሁሉ የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ። እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን። ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ እንመሰክር ዘንድ አዘዘን። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል» (የሐዋርያት ሥራ 10፡1-20፥ 34፥43)።

ምናልባትም የሚከተለው ገለጻ መረዳታችንን ይጨምርልን ይሆናል። ያለ መስኖ አንድ በረሃማ ስፍራ ውኃ ሊያገኝ አይችልም፤ እናም ግድብ ይገደባል። ይሁንና ያለ ቧንቧዎች ወይም ቦዮች ውኃው ከማጠራቀሚያው ወደ መስኮች ሊፈስ አይችልም። እንደዚሁም ሕይወትን ለሚሰጠው ውኃ ቧንቧዎቹ አይሁዶች ነበሩ። ክርስቶስ ራሱን የሕይወት ውኃ ብሎ ጠርቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያትም ዓለሙን ለሚወክሉ መስኮች ውኃን የሚያደርሱ የመጨረሻዎቹ የውኃ መተላለፊያዎች ናቸው።

ኢየሱስ በሕይወት ዘመኑ ለመስኮች ውኃ የሚያደርሱ ቧንቧዎች ማዘጋጀቱ አግባብ ያለው ነገር ነው። ይህም ሕይወቱን ከሞቱ አጅግ በተለየ ሁኔታ ዓለም- አቀፋዊ ያደርገዋል። በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ክርስቶስ በሮማዊ የመቶ አለቃ ውስጥ ትልቅ እምነት ስለ ተመለከተ እንዲህ አለ፡-

> «እውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም። እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ የመንግሥት ልጆች (አይሁዶች) ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ» (ማቴዎስ 8፡10-12)።

ሥራው ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ፥ ታላቁ ተልዕኮ በመባል የሚታወቀውን የመጨረሻ ትእዛዝ ሰጠ፡-

> «ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴዎስ 28፡19-20)።

ለሙስሊሙ ሱራህ 21፡91ን ማንበብ የበለጠ ማረጋገጫ ይሆንለታል፡- «እርሷንም ልጅዋንም (ኢየሱስ) (እንደዚሁ)፥ ለዓለማት ታምር ያደረግናትን (መርየምን አስታውስ)።»



# በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መሐመድ እንደ ተተነበዩ ሆነው የቀረቡ ትንቢቶች

ቁርአን እንደሚከተለው ይናገራል፡-

1. «የመርየም ልጅ፥ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፍቴ ያለውን የማረጋገጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ፥ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን፥ ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ» (ሱረቱ 61፡6)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ዘገባ እናገኛለን?

አሕመድ መሐመድ ከሚለው ጋር አንድ ዓይነት ስም ሲሆን፥ የሁለቱም ትርጉም «የተመሰገነ» ማለት ነው። ይህ በግሪክ ቋንቋ «ጰራክሌቶስ» እንደ ሆነ ተነግሮናል። በዮሐንስ ወንጌል 14፡16 ላይ የሚከተለውን እናገኛለን፡-

> «እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ ጰራክሌቶስ (አጽናኝ ወይም አማካሪ) ይሰጣችኋል።»

በቁርአን ምንባብ በመደገፍ፥ ሙስሊሞች ይህ ጥቅስ ከዚህ በላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ በግልጽ የተተነበየውን የመሐመድን መምጣት ለማድበስበስ በፈለጉ ክርስቲያኖች የተዘጋጀ ማጭበርበሪያ ነው ብለው ይናገራሉ። ዳሩ ግን ከመሐመድ መምጣት በብዙ መቶ ዓመታት ወደ ኋላ የሚርቁት የዚህ የዮሐንስ ወንጌል መዛግብት ሁሉ «ጴራክሌቶስ» የሚለውን ቃል እንጂ «ጴርክሉቶስን» ይዘው እንደማይገኙ መግለጽ አለብን። ቀጣዩ ቁጥር (ጴርክሌቶስ»፡-

> «እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ (ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት) ዘንድ ስለሚኖር፥ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ»

በማለት ይገልጽልናል።

ስለ ሆነም መሐመድን በመንፈስ ቅዱስ ቦታ የሚያስቀምጥ ማንኛውም ትርጓሜ ከእውነት ጋር ኅብረት እንደ ሌለው ግልጽ ሊሆን ይገባል።